*M, m* (ኤም፡)
በእንግሊዝኛ አስራ ሶስተኛው ፊደል

*machine* (መ'፡ሺ'ን)
ማሽን/አንድን ነገር ለመስራያነት
የሚያገለግል መሣሪያ/
Dad has bought a machine to cut the grass.
አባዬ ሣሩን ለማጨጃ ማሽን ገዝቷል።



*mad* (ማድ)
እብድ/አዕምሮው ትክክል ያልሆነ/
ቀውስ
The mad dog bit the boy.
እብዱ ውሻ ልጁን ነከሰው።

*magazine* (ማገ'ዚ፡ን)
መጽሄት/ስለተለያዩ ጉዳዮች
የሚፃፍበት በወር ወይም በሳምንት
የሚታተም ፅሁፍ/
My brother gets sport magazine every month.
ወንድሜ የስፖርት መጽሄት
በየወሩ ያገኛል።

*magic* ('ማጂክ)
[redacted]
The thief disappeared by magic.
ሌባው በአስማት ተሰወረ።

*magnet* ('ማግኒት)
ማግኔት/ብረት ነገሮችን በሙሉ
ወደራሱ የሚጎትት ብረት/ መግነጢስ
Lula picked the pins up with a magnet.
ሉላ ስፒሎችን በማግኔት አነሳቻቸው።



*mail* (ሜይል)
ደብዳቤ/ሰላምታን ወይም መልእክትን
ለሌላ ሰው ፅፈን የምንልከው
I will pick up the mail at the post office today.
ዛሬ ከፖስታ ቤት ደብዳቤዎች
አመጣለሁ።



*maize* (ሜይገዝ)
[redacted]
Maize is an important food in Africa.
በቆሎ በአፍሪካ ተፈላጊ ምግብ ነው።



*make* (ሜይክ)

1. አንድ ነገር መስራት

Birhanu will make a boat out of wood and paper.

ብርሃኑ ከእንጨትና ከወረቀት ጀልባ ሊሰራ ነው።

2. አንድ ነገር እንዲያደርጉ ማድረግ

You made me go to bed early last night.

ባለፈው ምሽት በጊዜ እንድተኛ አደረግኸኝ።

*male* (ሜይል)

ተባእት/የማንኛውም እንስሣ ወንድ/

Men and bulls are both male.

ወንድ ሰውና ኮርማ ሁለቱም ወንዶች ናቸው።

*mammal* (ማመል)

ጡት የሚያጠቡ እንስሳት

Whales, cows and dogs are mammals.

አሳነባሪዎች ፣ላሞችና ውሾች አጥቢ እንስሳት ናቸው።





*man* (ማን)

ወንድ/ሰው

My father is a man but my mother is a woman.

አባቴ ወንድ ነው እናቴ ግን ሴት ናት።



(ማነ)

ፀባይ

The girl has good manner.

ልጅቷ ጥሩ ፀባይ አላት።

(ሜኒ)

ብዙ

There are many elephants in Africa.

በአፍሪካ ውስጥ ብዙ ዝሆኖች አሉ።

(ማፕ)

ካርታ/የመሬትን የተለያዩ ክፍሎች የሚያሳይ ስዕል/

Can you find Ethiopia on the map?

ኢትዮጵያን በካርታ ላይ ማግኘት ትችላለህ?



(ማ:ች)

መጋቢት/በጎርጎርሣውያን የአመቱ 3ኛ ወር በኢትዮጵያውያን የአመቱ 7ኛ ወር/

March comes after February.

መጋቢት ከየካቲት ቀጥሎ ይመጣል።

*march* (ማ:ች)
ለወታደሮች ተሰልፎ መሄድ
The soldiers marched down the street.
ወታደሮቹ ተሰልፈው በመንገዱ ሄዱ።

*mark* (ማ:ክ)
1. ምልክት/አንድ ነገር ላይ ያለ ለየት ያለ ነገር/
You have a dirty mark on your shirt.
ሸሚዝህ ላይ ቆሻሻ ምልክት አለብህ።
2. ፈተና ታርሞ የሚሰጥ ውጤት
My sister got good mark in English exam.
እህቴ በእንግሊዝኛ ፈተና ጥሩ ውጤት አገኘች።

*market* ('ማ:ኪ.ት)
ገበያ/ሰዎች እቃዎችን የሚገዙበትና የሚሸጡበት ቦታ/
My mother always buys fruits in the market.
እናቴ ሁልጊዜ ከገበያ ፍራፍሬዎችን ትገዛለች።

*marmalade* ('ማ:መሌይድ)
ማርማላት/ከተፈጨ ፍራፍሬዎችና ከስኳር የሚሰራ ጣፋጭ ምግብ/
My father is going to make orange marmalade.
አባቴ የብርቱካን ማርማላት ሊሰራ ነው።

*marry* ('ማሪ)
ባል ወይም ሚስት ማግባት
My sister is going to marry tomorrow.
እህቴ ነገ ልታገባ ነው።

*mask* (ማ:ስክ)
ጭምብል/ፊትን የሚሸፍን ነገር
The man with the gun was wearing a mask.
ባለ ጠመንጃው ሰውዬ ጭምብል አጥልቆ ነበር።



*mast* (ማ:ስት)
እንጨት/የባንዲራ መስቀያ አይነት ረጅም ብረት/
The mast broke and the ship's sail fell down.
ቋሚው እንጨት ተሰበረና የመርከቧ ሸራ ወደቀ።

*master* ('ማስተ)
ሃላፊ/ የአንድ ነገር ባለቤት/
The dog followed his master.
ውሻው ባለቤቱን ተከተለ።

*mat* (ማት)
ምንጣፍ/ መሬት ላይ የሚነጠፍ ከክር ወይም ከሣር የሚሰራ ነገር ስጋጃ/ ሰሌን
My mother lays mat on the floor in winter.
በክረምት እናቴ ወለሉ ላይ ምንጣፍ ታነጥፋለች።



*match* (ማች)

1. በሁለት ቡድኖች መሀል የሚደረግ የስፖርት ግጥሚያ

The football match will be played on Saturday.

የእግር ኳስ ግጥሚያው ቅዳሜ ይደረጋል።

2. ክብሪት

I need a match to light the fire.

እሣቱን ለማያያዝ ክብሪት ያስፈልገኛል።



*material* (መ'ቲየሪየል)

አንድ እቃ ወይም ልብስ የተሰራበት ነገር/ቁስ

That material is leather. I will use it to make shoes.

ያ ነገር ቆዳ ነው። ጫማ ለመስሪያነት እጠቀምበታለሁ።



*mathematics* (ማተ'ማቲክስ)

የሂሣብ ስሌት/ሂሣብ ቁጥሮችን የምና ሰላበት/ ሒሳብ

My father teaches Mathematics.

አባቴ ሂሣብ ያስተምራል።

*matter* (ማተ/ር) ስ-

1. ነገር/ጉዳይ

What is the matter?.

ጉዳዩ ምንድን ነው?

2. ቁስ አካል

We can see and touch a matter.

ቁስ አካልን ማየትና መዳሰስ እንችላለን።

*mattress* ('ማትረስ)

ፍራሽ/ በተለያዩ ነገሮች የሚሞላ ለመተኛ የሚያገለግል

They filled the mattress with the straw.

ፍራሹን በጭዱ ሞሉት።



*May* (ሜይ)

ግንቦት/በጎርጎርሣውያን የአመቱ 5ኛ ወር በኢትዮጵያውያን የአመቱ 9ኛ ወር/

June is the month after May.

ሰኔ ከግንቦት በሁዋላ ያለ ወር ነው።

*may* (ሜይ)

እርግጠኛ ያልሆኑበት ነገር /ምናልባት ሊሆን ይችላል የሚሉት/

He may come today.

ዛሬ ሊመጣ ይችላል።

*meal* (ሚል)
አንዱ ቀርቦ የሚበላ ምግብ ቁርስ፣ ምሣ ወይም እራት
We will have our evening meal when our father comes home.
አባታችን እቤት ሲመጣ እራታችንን እንመገባለን።

*meaning* (ሚ:ኒን)
ፍቺ ወይም ትርጉም
What is the meaning of matter?
የቁስ አካል ትርጉሙ ምንድነው?

*measles* (ሚ:ዝልዝ)
ኩፍኝ
My brother is ill. He has measles.
ወንድሜ ታሟል ኩፍኝ ይዞታል።

*measure* (ሜዠር)
የአንድን ነገር መጠን ትልቅነት ወይም ትንሽነት ለማወቅ በሜትር ወይም በኪሎ መለካት/ልኬት
Mom is measuring my brother for making him new trousers.
እማዬ ለወንድሜ አዲስ ሱሪ ልትሰፋለት እየለካችው ነው።



*meat* (ሚ:ት)
ስጋ/የእንስሳት አካል የተሠራበት ነገር/
I need two kilograms of meat for the stew.
ለወጥ መስሪያ ሁለት ኪሎ ስጋ እፈልጋለሁ።



*medicine* (መ'ዲስን)
አንድ ሰው ሲታመም ሃኪሙ የሚሰጠው መድሃኒት
My sister took her medicine.Now she felt better.
እህቴ መድሃኒቷን ወሰደች። አሁን ተሽሏታል።



*meet* (ሚ:ት)
አንድ ቦታ መገናኘት
I will meet you at Sheraton.
ሸራተን አገኝሃለሁ።

*memory* (ሜመሪ)
አንድ ያለፈን/የቆየን ነገር መናገር አለመርሣት የማስታወስ ችሎታ/
The old man has a good memory.
ሽማግሌው ጥሩ የማስታወስ ችሎታ አላቸው።

*mend* (ሜንድ)
መጠገን/ አንድ የተበላሸ የማይሰራ ነገር መልሶ እንዲሰራ ማድረግ/
Dad mended the broken chair.
አባዬ የተሰበረውን ወንበር ጠገነው።

*merry* ('ሜሪ)
ደስተኛ መሆን
The children walked down the road singing merrily.
ህፃናቱ በደስታ እየዘመሩ በመንገዱ ሄዱ።

*mess* (ሜስ)
በስነስርአቱ ያልተቀመጠ/ የተዘበራረቀ/ የቆሸሸ
My brother's room is always in a mess.
የወንድሜ ክፍል ሁሌ እንደተዘበራረቀ ነው።

*message* ('ሜሲጅ)
መልእክት/አንድ ሰው ለሌላ ሰው እንድንነግር የሚነገረን ነገር
The teacher gave me a message to my mother.
መምህሩ ለእናቴ የማደርሰው መልእክት ሰጠኝ።


*messenger* ('ሜሰንጀ)
መልእክተኛ/መልእክት የሚያመላልስ ሰው/
The messenger took the letter to the post office.
መልእክተኛው ደብዳቤውን ወደ ፖስታ ቤት ወሰደው።

*metal* ('ሜትል)
ብረታ ብረት/ብረት የሆኑ ነገሮች በሙሉ
Gold, silver and iron are all metals.
ወርቅ ብርና ብረት ሁሉም ብረታ ብረት ናቸው።

*metre* (ሚ:ተ)
ሜትር/የአንድ ነገር ቁመት መለኪያ/
A very tall man could be two metres in height.
በጣም ረጅም ሰው ቁመቱ ሁለት ሜትር መሆን አለበት።

*microphone* ('ማይክረፈውን)
ድምፅ ማስተላለፊያ መሳሪያ/መቅጃ
The President used a microphone to speak to the crowd.
ፕሬዝዳንቱ ለህዝቡ በድምፅ ማጉያው ንግግር አደረጉ።

*microscope* ('ማይክረስከውፐ)
አጉይ መነፅር /አንድን ነገር ከፍ አድርጎ የሚያሣይ መሣሪያ
The ant seems huge under the microscope.
በአጉይ መነፅር ሲታይ ጉንዳኑ ግዙፍ ይመስላል።



*middle* (ሚድል)
**መሃከለኛ/ከሁለት ነገሮች መሃከል ያለ ነገር/**
The children were playing in the middle of the field.
**ልጆቹ በሜዳው መሃከል ሲጫወቱ ነበር።**

*midnight* (ሚድናይት)
**እኩለ ሌሊት/ጨለማው በጣም ሃይለኛ (ድቅድቅ) የሚሆንበት ጊዜ/**
I went to bed at midnight.
**እኩለ ሌሊት ሲሆን ተኛሁ።**

*milk* (ሚልክ)
**ወተት/ ከላም የሚገኝ ነጭ ፈሳሽ/**
I drink a litre of milk everyday.
**በየቀኑ አንድ ሊትር ወተት እጠጣለሁ።**



*million* (ሚልየን)
**ስድስት ዜሮዎች ያሉት ቁጥር**
1 ሚሊዮን (1000,000)
I would love to have a million Birr.
**አንድ ሚሊዮን ብር ቢኖረኝ ደስ ይለኛል።**

*mince* (ሚንስ)
**መፍጨት/ስጋን በትንንሹ መከተፍ/**
My mother minces the meat to make stew.
**እናቴ ወጥ ለመስራት ስጋውን በትንንሹ ትከትፈዋለች።**

*mind* (ማይንድ)
**አእምሮ/ለማሰብ የምንጠቀምበት የጭንቅላታችን ክፍል/**
Everything you learn goes into your mind.
**የምትማረው ነገር ሁሉ ወደ አእምሮህ ይሄዳል።**

*mine* (ማይን)
**የከበሩ ድንጋዮችን/ ማዕድን ለማውጣት የሚቆፈርበት ቦታ/**
My uncle works in a gold mine.
**አጎቴ በወርቅ ማዕድን ማውጫ ውስጥ ይሠራል።**

*minute* (ሚኒት)
**የሰአት መለኪያ**
There are sixty minutes in an hour.
**በአንድ ሰአት ስልሣ ደቂቃዎች አሉ።**

*mirror* (ሚረ)
**መስታወት/ሲመለከቱት ራስን መልሶ የሚያሳይ/**
I can see my face in the mirror.
**ፊቴን በመስታወት ማየት እችላለሁ።**



*mischief* (ሚስቺፍ)
**ተንኮል/ጥሩ ያልሆነ ሌሎችን የሚጎዳ ስራ/**

Abebe is a bad boy. He always gets in to mischief.
አበበ መጥፎ ልጅ ነው። ሁልጊዜ ተንኮል ይሠራል።

*miss* (ሚስ)
1. ማግኘት የሚችሉትን ነገር ማጣት/ ሳያገኙ መቅረት/ማምለጥ/
I missed the bus and had to walk home.
እውቶብሱ ስላመለጠኝ ወደ ቤት በእግሬ መሄድ ነበረብኝ።
2. መናፈቅ/የሄደን ሰው/ ነገር ለማየት መጓጓት
I miss you.
ናፍቀኸኛል።

*mistake* (ሚ'ስቴይክ)
ስህተት
There are six spelling mistakes in this sentence.
በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ስድስት የቃላት ግድፈቶች አሉ።

*mix* (ሚክስ)
መቀላቀል/የተለያዩ ነገሮችን በንድ ላይ ማድረግ/
Sisay helped his mother mix the things for the cake.
ሲሳይ እናቱን ለኬክ የሚያስፈልጉ ነገሮችን በመቀላቀል አገዛት።

*mixture* ('ሚክስቸ)
ድብልቅ/ከተለያዩ ነገሮች ተቀላቅሎ የሚሠራ/
Purple is a mixture of red and blue.
ወይንጠጅ ቀለም የቀይና የሰማያዊ ድብልቅ ነው።

*Monday* (መንዴይ)
ሰኞ/የሳምንቱ ሁለተኛ ቀን/
My sister washes her clothes on Mondays.
እህቴ ሰኞ ሰኞ ልብሶቿን ታጥባለች።

*money* ('መኒ)
ገንዘብ/አንድ ነገር የምንገዛበት ከወረቀት ወይም ከሣንቲም የተሠራ/
Mom gives us money every week to buy sweets.
እማዬ በየሣምንቱ ከረሜላ መግዣ ገንዘብ ትሰጠናለች።




*monkey* ('መንኪ)
ዝንጀሮ/ከእንስሣት ሁሉ ሰው የሚመስል እንስሣ/
The monkeys are swinging in the branches of the trees.
ዝንጀሮዎቹ የዛፎቹ ቅርንጫፎች ላይ እየተወዛወዙ ነው።



*monster* ('ሞንስተ)
ጭራቅ /በተረት የሚነገሩ እጅግ
አስፈሪ ፍጥረታት/
The children love to hear stories about monsters.
ልጆቹ ስለ አስፈሪ ፍጥረታት ታሪክ
መስማት ይወዳሉ።

*month* (መንስ)
ወር/ በኢትዮጵያ 13 ወራት አሉ።
ጳጉሜ ብቻ 5 1/4 ቀናት ሲኖሩት
ሌሎቹ 30 ቀናት አሏቸው።
በጎርጎርሣውያን 12 ወራት አሉ።
አንዳንዴ 29፣30 ወይም 31 ቀናት
ይይዛሉ።
The baby is three months old.
ህፃኑ 3 ወሩ ነው።

*moon* (ሙ:ን)
ጨረቃ/ቀኑ ሲጨልም ሰማይ ላይ
የምትታየው ትልቋ ብርሃን/
Sometimes the moon is round .
አንዳንዴ ጨረቃ ክብ ትሆናለች።




*mop* (ሞፕ)
መወልወያ/የቤት ውስጥ ወለል ማጠቢያ
ስሩ ጨርቅ ሆኖ እጀታ ያለው/
Our maid washed the floor with the mop.
ሰራተኛችን በመወልወያ ወለሉን
አጠበችው።



*more* (ሞ:)
ካለው ላይ መጨመር/ተጨማሪ
I would like some more stew.
ተጨማሪ ወጥ እፈልጋለሁ።

*morning* ('ሞ:ኒን)
ጠዋት/ጨለማው አብቅቶ ገና ብርሃን
መሆን ሲጀምር/
We leave for school at seven o'clock every morning.
ወደ ትምህርት ቤት ጠዋት ጠዋት
በአንድ ሰአት እንሄዳለን።

*mosque* (ሞስክ)
መስጊድ
Mosque is a holy place where the Moslems go to pray.
መስጊድ ሙስሊሞች ፀሎት
የሚያደርጉበት የተቀደሰ ስፍራ ነው።




*moth* (ሞስ)
የእሳት እራት/ቢራቢሮ የምትመስል ነፍሳት
Moths like to fly around lights at night.
የእሳት ራቶች ማታ ማታ በብርሃን ዙሪያ መብረር ይወዳሉ።



*mother* ('መዘ/ር)
እናት
My mother is an Engineer.
እናቴ መሀንዲስ ናት።

*motor* ('መውተ)
አንድን መሳሪያ የሚያንቀሳቅስ የመሣሪያው አካል
I need a new motor for the sewing machine.
ለልብስ መስፊያ መኪናዬ አዲስ ሞተር እፈልጋለሁ።



*mountain* ('ማውንቴን)
ተራራ/ከሌላው መሬት በጣም ከፍ ያለ ያበጠ መሬት/
My mother likes climbing a mountain.
እናቴ ተራራ መውጣት ትወዳለች።



*mouse* (ማውስ)
አይጥ/በየቤቱ ጥጋ ጥግ ጉድጓድ ቆፍራ የምትኖር ትንሽ እንስሳ/
The mouse chewed a hole in the kitchen door.
አይጧ በማእድ ቤቱ በር ላይ ቀዳዳ በሳች።



*mouth* (ማውስ)
አፍ/ምግብ የምናስገባበትና የምንነጋገርበት የሰውነት ክፍል/
The boy had too much food in his mouth so he could not speak.
ልጁ በአፉ ብዙ ምግብ ስለነበረ መናገር አልቻለም።

*move* (ሙ:ቭ)
1. ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መሄድ
We are moving into our new house today.
ዛሬ ወደ አዲሱ ቤታችን እንሄዳለን።
2. አንድን ነገር ከቦታው ማንቀሳቀስ ማንሣት

Please move that chair away from the window.
እባክህ ያንን ወንበር ከመስኮቱ አጠገብ አንሣው።

*much* (መች)
ብዙ
Did you get much rain last year?
ባለፈው ዓመት ብዙ ዝናብ አግኝታችሁ ነበር?

*mud* (መድ)
ጭቃ/ከውሃ የተቀላቀለ አፈር
The hippopotamus rolled in the mud.
ጉማሬው ጭቃው ላይ ተንከባለለ።

*mug* (መግ)
ትልቅ ኩባያ
I would love a mug of tea.
ሻይ በኩባያ ባገኝ ደስ ይለኛል።



*mule* (ምዩ:ል)
በቅሎ/ከፈረስና ከአህያ የምትወለድ እንስሳ/
The mule pulled the cart slowly up the hill.
በቅሎዋ ጋሪውን በዝግታ ወደ ተራራው ጎተተችው።



*multiply* ('መልቲፕላይ)
ማባዛት/አንድን ነገር ብዙ ማድረግ/
If you multiply twelve by three you will get thirty six.
አስራ ሁለትን በሶስት ብታባዛው ሰላሣ ስድስት ታገኛለህ።

*muscle* ('መስል)
ጡንቻ/ስፖርት ሲሰራ እጅና እግር ላይ የሚፈጠር ጠንካራ ስጋ/
The runner has very strong muscles in his legs.
ሯጩ በጣም ጠንካራ የእግር ጡንቻዎች አለው።



*museum* (ምዩ'ዚየም)
ቤተ መዘክር/የአንድ አገር ወይም ህዝብ ጥንታዊ ታሪኮች የሚቀመጡበት ቦታ/
Our class is going to the museum to see the old guns and spears.
የኛ ክፍል ጥንታዊ ጠመንጃዎችንና ጦሮችን ለማየት ወደ ቤተ መዘክር ይሄዳል።

*must* (መስት)
የግድ/በምንም አይነት የማይቀር ነገር መደረግ ያለበት ነገር/
You must get your hair cut today.
ዛሬ ፀጉርህን የግድ መቆረጥ አለብህ።

*mystery* ('ሚስተሪ)
ሚስጥር/ግራ የሚያጋባ/ምክንያቱ የማይታወቅ ነገር ወይም ድርጊት/
It's a mystery why she run away.
ለምን እንደኮበለለች ግራ የሚያጋባ ነገር ነው።

# Nn

*N, n* (ኤን)
14ኛው የእንግሊዝኛ ፊደል

*nail* (ኔይል)
1. ጥፍር/ የእግርና የእጅ ጣቶች ጫፍ ላይ ያለ ጠንካራ ሽፋን
The baby needs her nails cut.
ህፃኗ ጥፍሯን መቆረጥ ያስፈልጋታል።



2. ምስማር/ ቀጭን ከላዩ ጠፍጣፋ ብረት/
I need some nails to fix the fence.
አጥሩን ለመጠገን ጥቂት ምስማሮች እፈልጋለሁ።




*naked* (ኔይኪድ)
እራቁት/ ምንም ልብስ ሳይለብሱ
The naked children are playing in the river.
እራቁታቸውን የሆኑት ህፃናት ወንዙ ውስጥ ይጫወታሉ።



*name* (ኔይም)
ስም/የአንድ ነገር መጠሪያ
My name is Ojulu and I live in Arat Killo.
ስሜ ኦጁሉ ነው የምኖረውም አራት ኪሎ ነው።

*narrow* (ናረው)
ጠባብ/ ሰፊ ያልሆነ/
There is a narrow path between the houses.
ከቤቶቹ መሃል ጠባብ መተላለፊያ አለ።



*nasty* (ናስቲ)
1. መጥፎ/ ጥሩ ያልሆነ/
What is that nasty smell?
መጥፎው ሽታ ምንድነው?
2. በጣም የቆሸሸ
Who made that floor nasty?
ማነው ወለሉን ያቆሸሸው?

***nation*** ('ኔይሽን)
የአንድ አገር ነዋሪዎችና አገሪቷ
The president spoke to the nation on the radio.
ፕሬዝዳንቱ ለህዝቡ በሬዲዮ ንግግር አደረጉ።

***nature*** ('ኔይቸ/ር)
ተፈጥሮ/ እፅዋት፣ እንስሳት፣ ባህር፣ አየር፣ መሬት በሙሉ
Wild animals are part of nature.
የዱር እንስሳት የተፈጥሮ አካል ናቸው።

***naughty*** (ኖ፡ቲ)
ረባሽ/ መጥፎ ፀባይ ያለው
The teacher sent the naughty boy home .
መምህሩ ረባሹን ልጅ ወደ ቤቱ ላኩት።

***navy*** (ናይቪ)
1. የባህር ሃይል/የባህር ላይ ወታደር
My brother is a navy captain.
ወንድሜ የባህር ሀይል ካፒቴን ነው።
2. ደማቅ ሰማያዊ ቀለም
He was wearing a navy suit.
እሱ ደማቅ ሰማያዊ ሸሚዝ ለብሶ ነበር።

***near*** (ኒየ)
ቅርብ/ አጠገብ/ አቅራቢያ
I live near the school.
የምኖረው ከትምህርት ቤቱ አቅራቢያ ነው።

***nearly*** ('ኒየሊ)
በጣም የቀረበ የተጠጋ/ለትንሽ/
The bus nearly hit the car.
አውቶብሱ ለትንሽ መኪናውን ሊገጨው ነበረ።

***neat*** (ኒ፡ት)
ንፁህ/ ያልቆሸሸ
My clothes are always neat.
ልብሶቼ ሁሌ ንፁህ ናቸው።

***neck*** (ኔክ)
አንገት/ ከጭንቅላትና ከትከሻ መሃል ያለው አካል
Giraffe has a very long neck.
ቀጭኔ በጣም ረጅም አንገት አላት።

***need*** (ኒ፡ድ)
መፈለግ/የአንድ ነገር ማስፈለግ
I have a headache, I need to got to the doctor.
ራሴን አሞኛል ወደ ሃኪም መሄድ ያስፈልገኛል።

***needle*** (ኒ፡ድል)
1. መርፌ/ቀጭን አንዱ ወገን ሹል የሆነ በሌላው ወገን ቀዳዳ ያለው ብረት
My mother saw my shirt with a needle.
እናቴ ሸሚዜን በመርፌ ሰፋችልኝ።
2. የልብስ መስፊያ/ ሹራብ መስሪያ ብረት
My mother bought a knitting needle to make a sweater.
እናቴ ሹራብ ለመሥራት የሹራብ መስሪያ ብረት ገዛች።



*Neither ...nor* (ናይዘ... ኖ፡/ር)
ይሄኛውም ያኛውም አይደለም
Neither mother nor father can drive a car.
እናቴም አባቴም መኪና መንዳት አይችሉም።

*nephew* (ኔፊው)
የወንድም ወይም የእህት ወንድ ልጅ።
My nephew lives in Gondar.
የእህቴ ልጅ ጎንደር ይኖራል።

*nervous* (ነ፡ቨስ)
ቶሎ የሚፈራ/ የሚርበተበት
The horse is very nervous.
ፈረሱ እርብትብት ነው።

*nest* (ኔስት)
የወፎች የአይጦች ወይም የሌሎች እንስሳት ጎጆ ቤት
Birds make nests for their babies.
ወፎች ለልጆቻቸው ጎጆ ይሰራሉ።



*net* (ኔት)
መረብ/ በተቀጣጠሉ ቀጫጭን ገመዶች የሚሠራ
The fisherman caught a lot of fish in his net.
አሳ አጥማጁ በመረቡ ብዙ አሳዎችን አጠመደ።



*never* (ኔቨ/ር)
ፈጽሞ/ ለአንዴም እንኳን የማይሆን
We never go to school on Sundays.
እሁድ እሁድ ፈጽሞ ወደ ትምህርት ቤት አንሄድም።

*new* (ንዩ፡)
አዲስ/ገና የተገዛ የተገኘ ወይም የተሠራ ነገር
Mother bought us a new football.
እማዬ አዲስ የእግር ኳስ ገዛችልን።

*news* (ንዩ፡ዝ)
ዜና/ስለተደረገ አዳዲስ አስገራሚ ነገሮች የሚነገር ፣የሚፃፍ ቃል
Did you hear the news about the new baby?
ስለ አዲሱ ሕፃን ዜና ሰማህ?

*next* (ኔክስት)
ቀጥሎ/ከአንድ ነገር ቀጥሎ ያለው

I can't go this week, but I can go next week.
በዚህ ሣምንት አልሄድም በሚቀጥለው ሣምንት እሄዳለሁ።


*nib* (ኒብ)
የብዕር ጫፍ
A pen without a nib is useless.
ጫፉ የሌለው ብእር ጥቅም የለውም።



*nice* (ናይስ)
ጥሩ
That nice boy helped me to carry the big box.
ያ ጥሩ ልጅ ትልቁን ሣጥን ለመሸከም ረዳኝ።


*niece* (ኒ:ስ)
የወንድም/የእህት ሴት ልጅ
Aster is my niece.
አስቴር የወንድሜ ልጅ ናት።

*night* (ናይት)
የጭለማ/ የምሽት ጊዜ
I went to bed early last night.
ትላንት ማታ ቶሎ ተኛሁኝ።



*nightmare* ('ናይትሜየ)
ቅዠት/አስፈሪ መጥፎ ህልም
My sister had a nightmare. She woke up crying.
እህቴ መጥፎ ህልም አይታ እያለቀሰች ከእንቅልፏ ነቃች።

*nine* (ናይን)
ዘጠኝ ቁጥር /9/
I like number nine.
ዘጠኝ ቁጥርን እወዳታለሁ።



*nineteen* (ናይን'ቲ:ን)
አስራ ዘጠኝ/19/
I have to milk nineteen cows everyday.
በየቀኑ 19 ላሞች ማለብ አለብኝ።

*ninety* ('ናይንቲ)
ዘጠና /90/
There must be ninety elephants in that herd.
በመንጋው ውስጥ ያሉት ዘጠና ዝሆኖች መሆን አለባቸው።

*nip* (ኒፕ)
ነከስ ወይም ቆንጠጥ 'ማድረግ
The dog nipped me with its teeth.
ውሻው በጥርሶቹ ነከስ አደረገኝ።

*no* (ነው)
አይ አይሆንም/አይደለም ማለት

You must learn to say "no" sometimes.
አንዳንድ ጊዜ "አይሆንም" ማለትን መማር አለብህ።

*nobody* (ነውበዲ)
ምንም ወይም ማንም ሰው
I shouted but there was nobody there.
ጮህኩኝ ግን ማንም ሰው አልነበረም።

*nod* (ኖድ)
መስማማትን ለመግለፅ ራስን ወደላይ ወደታች ማወዛወዝ
I saw him nod his head to say yes.
አዎ ለማለት ራሱን ሲያወዛውዝ አየሁት።

*noise* (ኖይዝ)
ጫጫታ/የብዙ ነገሮች/ ሰዎች ድምጽ በአንድነት
The people watching the football match made a lot of noise.
ኳስ ጨዋታ የሚያዩት ሰዎች በጣም ተንጫጩ።

*none* (ነን)
ምንም/ባዶ
I have five books. My brother has none.
እኔ አምስት መጻህፍት አሉኝ ወንድሜ ግን ምንም የለውም።

*noon* (ኑ፡ን)
ቀትር ልክ ከቀኑ ስድስት ሰአት
The sun is high in the sky at noon.
ልክ በስድስት ሰአት ፀሃይ በሰማይ ላይ ርቃ ትታያለች።

*north* (ኖ፡ዝ)
የሰሜን አቅጣጫ
Europe lies to the north of Africa.
አውሮፓ በአፍሪካ በስተሰሜን ይገኛል።



*nose* (ነውዝ)
አፍንጫ/የምናሽትበት የሰውነት አካል
We use our nose to smell things.
አፍንጫችንን ነገሮችን ለማሽተት እንጠቀምበታለን።



*note* (ነውት)
1. አጭር ደብዳቤ ወይም ማስታወሻ
Write a note to your uncle today.
ዛሬ ለአጎትህ ማስታወሻ ፃፍለት።
2. የወረቀት ገንዘብ/ ብር
The man paid fifty Birr notes for

the baskets.
ሰውየው ለቅርጫቶቹ ድፍን ሃምሣ ብር ከፈለ።

*nothing* ('ነሲን)
ምንም የሌለበት ባዶ
I opened the box but there was nothing in it.
ሳጥኑን ከፈትኩት ግን በውስጡ ምንም አልነበረም።

*notice* ('ነውቲስ)
1. ማስተዋል/ አንድን ነገር ወይም ድርጊት መሆኑን መኖሩን ማየት/
He did not notice the ball.
ኳሱን አላስተዋለውም።
2. ማስታወቂያ/ ሁሉም ሰው እንዲያየው የሚፃፍ ወረቀት/
The teacher put up the notice in the classroom.
መምህሩ የማስታወቂያ ወረቀቱን ክፍል ውስጥ አስቀመጡት።

*noun* (ናውን)
የሰው ወይም የቦታ ወይም የእቃ ስም
The word Fofi is a noun. It is the name of my son.
"ፎፊ" የሚለው ቃል ስም ነው። የወንድ ልጄ መጠሪያ ነው።

*November* (ነው'ቬምበ)
ሕዳር/በጎርጎርሣውያን የአመቱ 11ኛ ወር በኢትዮጵያውያን የአመቱ 3ኛ ወር
November comes after October.
ህዳር ከጥቅምት ቀጥሎ ይመጣል።

*now* (ናው)
አሁን/ በዚህ ሰአት
I want you to come with me now.
አሁን አብረኸኝ እንድትመጣ እፈልጋለሁ።

*number* ('ነምበ)
ቁጥር
1, 2, 3 and 4 are numbers.
፩፣ ፪፣ ፫ እና ፬ ቁጥሮች ናቸው።

*nurse* (ነ፡ስ)
ነርስ/የታመሙ ሰዎችን በመርዳት ሙያ የሰለጠነች የዶክተር ረዳት ሀኪም
My mother works in a hospital . She is a nurse.
እናቴ ነርስ ናት ሆስፒታል ውስጥ ትሰራለች።



*nut* (ነት)
ለውዝ/እቾሎኒ
I like to eat nuts.
ለውዝ መብላት እወዳለሁ።

# Oo

*O,o* (ኧው)
እስራ አምስተኛው የእንግሊዝኛ ፊደል

*oar* (ኦር)
የጀልባ መቅዘፊያ/ ረጅም ጫፉ ጠፍጣፋ እንጨት
The lazy man lost his oar.
ሰነፉ ሰው የጀልባውን መቅዘፊያ ጣለው።

*oasis* (ኧው'ኤይሲስ)
እጅግ ሞቃታማ በሆነ አካባቢ የሚገኝ ውሃና ዛፍ ያለበት ቦታ
They were nearly dead when they found the oasis.
ውሃ ያለበትን ቦታ ሲያገኙ ለመሞት ትንሽ ቀርቷቸው ነበር።

*obedient* (ኧ'ቢ፡ዲየንት)
ታዛዥ/የተባለውን ሁሉ የሚያደርግ እሺ የሚል/
My mother says the dog is very obedient.
እናቴ ውሻው በጣም ታዛዥ ነው ትላለች።

*obey* (ኧ'ቤይ)
መታዘዝ/ ትእዛዝ መቀበል የተነገረን ነገር እሺ ማለት
A soldier should obey orders.
ወታደር ትእዛዝ መቀበል አለበት።

*object* ('ኦብጂክት)
ዕቃ
That shop is full of lovely objects.
ያ ሱቅ ደስ በሚሉ ዕቃዎች የተሞላ ነው።

*occupation* (ኧክዩ'ፔይሽን)
የሥራ አይነት /የሚተዳደሩበት የሥራ መስክ
My father's occupation is teaching.
የአባቴ ሥራ አስተማሪነት ነው።

*ocean* ('ኧውሽን)
ውቅያኖስ/በጣም ብዙ ውሃ የተከማቸበት ቦታ/
The pacific is a huge ocean.
ፓስፊክ በጣም ትልቅ ውቅያኖስ ነው።




*o'clock* (አክሎክ)
ሰአት
Look! It is four o'clock.
ተመልከት አራት ሰአት ሆኗል።



*octagon* ('አክተገን)
ባለ ስምንት ማዕዘን ቅርፅ
He has drawn an octagon in his exercise book.

ዶብተሩ ላይ ባለ ስምንት መአዘን ቅርፅ ስዓል።



*October* (ኦክ'ቶውበ)
ጥቅምት/በጎርጎርሣውያን የአመት 10ኛ ወር በኢትዮጵያውያን የአመት 2ኛ ወር/
October is very cold in Ethiopia.
በኢትዮጵያ ጥቅምት በጣም ይበርዳል።

*octopus* (ኦክቶፐስ)
ስምንት እግሮች ያሉት አሣ
The octopus caught the fish in its arms.
ኦክቶፐሱ አሣውን በክንዶቹ ያዘው።



*odd* (ኦድ)
1. ከሌሎቹ ለየት ያለ ሰው/ ነገር /ድርጊት/
He looks odd in that huge hat.
ያንን ትልቅ ኮፍያ ሲያደርግ ለየት ያለ ነገር ይመስላል።
2. ጎዶሎ ቁጥሮች/ለሁለት የማይከፈሉ ቁጥሮች
1,3, 5,7 and 9 are all odd numbers.
1፣ 3፣ 5፣ 7 እና 9 ሁሉም ጎዶሎ ቁጥሮች ናቸው።

*offer* ('አፈ)
አንድን ነገር ለማድረግ ጥያቄ ማቅረብ
I will offer to take the children home.
ልጆቹን ወደቤት ለመውሰድ ጥያቄ አቀርባለሁ።

*office* ('አፊስ)
ቢሮ/ስራ የሚሰራበት ቤት ወይም ቦታ
Mimi is a typist. She works in an office.
ሚሚ ታይፒስት ናት ቢሮ ውስጥ ትሰራለች።



*officer* ('አፊሰ)
መኮንን/የወታደር ማዕረግ ከመቶ አለቃ በላይ/
The officer told the soldiers to stand still.
መኮንኑ ወታደሮቹን በተጠንቀቅ እንዲቆሙ ነገራቸው።

*often* ('አፍን)
ብዙ ጊዜ ማድረግ/አንድን ነገር በተደጋጋሚ/
I often play football with my father.

ብዙ ጊዜ ከአባቴ ጋር እግር ኳስ እጫወታለሁ።

*oil* (ኦይል)
1. የምግብ ዘይት/ከተክሎች የሚሠራ የሚበላ ፈሣሽ/
They roasted the meat in oil.
ስጋውን በዘይት ጠበሱት።
2. የመኪና ዘይት/ከመሬት ተቆፍሮ የሚገኝ ለመኪና ሞተር የሚጨመር ፈሣሽ/
Almaz bought a litre bottle of oil for her car.
አልማዝ ለመኪናዋ አንድ ሊትር ዘይት ገዛች።



*old* ('ኧውልድ)
አሮጌ/ብዙ ጊዜ ያገለገለ ነገር/
I like old cars.
አሮጌ መኪናዎች እወዳለሁ።

*on* ('ኦን)
1. በአንድ ነገር ላይ መሆን
Fofy is standing on the chair.
ፎፊ ወንበሩ ላይ ቆሟል።
2. መከፈት/ለኤሌክትሪክ እቃዎች በሥራ ላይ መሆን/ለመብራት ደግሞ መብራት
The radio is always on in his room.
በክፍሉ ውስጥ ሬድዮው ሁልጊዜ እንደተከፈተ ነው።
When I came in the light was on.
እኔ ስመጣ መብራቱ በርቶ ነበር።

*once* ('ወንስ)
አንዴ
My father meets the Prime Minister once in a year.
አባቴ ጠቅላይ ሚኒስትሩን በአመት አንዴ ያገኛቸዋል።

*one* ('ወን)
አንድ
I have one brother and one sister.
እኔ አንድ ወንድም እና አንድ እህት አለኝ።

*onion* ('ኧኒየን)
ቀይ ሽንኩርት
Cutting onions always makes me cry.
ሽንኩርት መክተፍ ሁልጊዜ ያስለቅሰኛል።

*only* ('ኧውንሊ)
1. ብቸኛ/አንድ ብቻ/ ሌላ ተጨማሪ የሌለው/
She is the only child in that family.
እሷ በዚያ ቤተሰብ ብቸኛ ልጅ ናት።
2. ብቻ/ ሌላ ተጨማሪ የሌለው
There are only three lemons.
ያሉት ሶስት ሎሚዎች ብቻ ናቸው።

*open* ('ኧውፐን)
አንድ የተዘጋን ነገር መክፈት
Please open the door. I want to go home.

እባክህ በሩን ክፈተው ወደቤት መሄድ እፈልጋለሁ።

*opposite* ('ኦፖዚት)

1. በሌላኛው አቅጣጫ

His house is on the opposite side of the road.

ቤቱ ከመንገዱ በሌላኛው አቅጣጫ ነው።

2. ተቃራኒ

Hot is the opposite of cold.

ሙቅ የቀዝቃዛ ተቃራኒ ነው።

*orange* ('ኦሬንጅ)

ብርቱካን/ጣፋጭ ክብ፣ ውስጡ ውሃ ያለው ፍሬ/

They made a cold drink from the oranges.

እነሱ ከብርቱካኖቹ ቀዝቃዛ መጠጥ ሰሩ።



2. ብርቱካንማ ቀለም

My sister is wearing an orange dress.

እህቴ ብርቱካንማ ቀሚስ ለብሳለች።

*orchard* ('ኦ:ቸድ)

የፍራፍሬ ተክል የሚያድግበት ቦታ/እርሻ

The boys stole the oranges from the orchard.

ልጆቹ ከፍራፍሬ እርሻው ብርቱካኖች ሰረቁ።



*orchestra* ('ኦ:ኪስትረ)

ኦርኬስትራ/አንድ ላይ ሆነው ሙዚቃ የሚጫወቱ ሰዎች ቡድን

My brother plays the 'kirar' in the orchestra.

ወንድሜ የሙዚቃ ቡድኑ ውስጥ ክራር ይጫወታል።



*order* (ኦ:ደ)

1. አንድ ነገር እንዲደረግ/ እንዲሰራ ትእዛዝ መስጠት


The teacher ordered us to stop talking.

አስተማሪዋ ዝም እንድንል አዘዘችን።

2. ቅደም ተከተል/አንድ ነገር የተሰራበት የተቀመጠበት ስርአት

Sit properly in your order.

በቅደም ተከተላችሁ በሥነ-ሥርዓት ተቀመጡ።



*ordinary* ('ኦ:ድንሪ)
ተራ/ከሌላው ምንም ልዩነት የሌለው የተለመደ
They are an ordinary family.
እነሱ ያው የተለመደው አይነት/ተራ/ ቤተሰቦች ናቸው።

*orphan* ('ኦ:ፍን)
የሙት ልጆች/አባትና እናታቸው የሞቱባቸው ልጆች
Senayt is an AIDS orphan.
ሰናይት በኤድስ ምክንያት ወላጆቿን ያጣች ልጅ ናት።

*ostrich* ('ኦስትሪች)
ሰጎን/ከወፎች ሁሉ ትልቁና የማትበረዋ ወፍ/
Ostriches are birds that cannot fly.
ሰጎኖች መብረር የማይችሉ ወፎች ናቸው።



*other* ('ኧዘ)
ሌላ/ሌላኛው
Don't take this book, take the other.
ይህን መጽሃፍ አትውሰድ ሌላኛውን ውሰድ።

*out* ('አውት)
ከቤት ወይም ከአንድ ቦታ ውጭ
I came to your house but you were out.
እቤትህ መጥቼ ነበር ነገር.ግን አንተ ወጥተህ ነበር።


*outside* (አውት'ሳይድ)
ውጭ
Let's go outside. It's very warm in the house.
ቤቱ በጣም ስለሚሞቅ ወደ ውጭ እንውጣ።

*oval* (ኧውቨል)
ሞላላ የእንቁላል አይነት ቅርጽ
The runners run round an oval track.
ሯጮቹ ሞላላ ቅርጽ ባለው የመሮጫ ስፍራ ሮጡ።



*oven* ('ኧቨን)
ምግብ ማብሰያ ምድጃ
My mother cooked the chicken in the oven.

እናቴ በምድጃው ውስጥ ዶሮውን ጠበሰች።



*over* ('ኦውቨ)
1. አንድ ድርጊት ሲያበቃ
The birthday party was over.
የልደት ግብዣው አብቅቶ ነበር።
2. መዝለል/በአንድ ነገር በላዩ ላይ ማለፍ መራመድ
The boys climbed over the fence.
ልጆቹ በአጥሩ ላይ ዘልለው አለፉ።


*owe* (ኦው)
ገና ያልከፈልነው ገንዘብ/ ለሌላ ሰው መክፈል የሚገባን
Ato Debela owe me a lot of money.
አቶ ደበላ ያልከፈሉኝ ብዙ ገንዘብ አለባቸው።

*owl* (አውል)
ጉጉት/ በጨለማ ማየት የምትችል በቀን ማየት የማትችል ወፍ
An owl is able to see in the dark.
ጉጉት በጨለማ ማየት ትችላለች።



*own* (ኦውን)
አለው/የራስ የሆነ ነገር
Alemu owns four cows and six goats.
አለሙ አራት ላሞችና ስድስት ፍየሎች አሉት።

*ox* (ኦክስ)
በሬ/ ወንድ የቀንድ ከብት
The farmer used his ox to plough the field.
ገበሬው መሬቱን ለማረስ በሬውን ተጠቀመበት።



*oyster* ('ኦይስተ)
1. ሰደፍ 2. የአሣ ዘር
Pearl is found in oyster.
ሉል የሚገኘው ከኦይስተር ውስጥ ነው።

***P,p*** (ፒ)
አስራ ስድስተኛው የእንግሊዝኛ ፊደል

***pace*** (ፔይስ)
የአንድ የትልቅ ሰው እርምጃ
It is ten paces to the tree.
እስከ ዛፉ ድረስ ርቀቱ አስር እርምጃ ነው።

***pack*** (ፓክ)
1. እቃን፣ ልብስን ሳጥን ወይም ካርቶን ውስጥ መክተት ለመሄድ
I will pack the clothes in the case.
ልብሶቹን ሻንጣ ውስጥ እከታተቸዋለሁ።
2. የውሾች መንጋ/አብረው የሚሄዱ ውሾች/
A pack of dogs chased the goats.
የውሾች መንጋ ፍየሎቹን አባረሩ።

***package*** (ፓኪጅ)
ጥቅል/ የተጠቀለለ የታሸገ ነገር
My sister sent me a package from the USA.
እህቴ የታሸገ ነገር ከ ዩ.ኤስ.ኤ ላከችልኝ።

***paddle*** (ፓድል)
መቅዘፊያ/ጀልባ ወደፊት እንዲሄድ ውሃው የሚቀዘፍበት ሜፉ ጠፍጣፋ እንጨት/
The boy paddled the canoc across the river.
ልጁ ጀልባውን በወንዙ ላይ ቀዘፈ።



***page*** (ፔይጅ)
ገጽ/የመጽሃፍ ወይም የደብተር አንዷ ወረቀት/
This book has fifty pages.
ይህ መጽሃፍ ሃምሳ ገጾች አሉት።

***pain*** (ፔይን)
ሰውነታችን ውስጥ የሚሰማን የህመም ስሜት
My mother gave me medicine for the pain in my head.
ለራሴ ህመም እናቴ መድሃኒት ሰጠችኝ።

***paint*** (ፔይንት)
ቀለም መቀባት
I will paint that wall blue.
ግድግዳውን ሰማያዊ ቀለም እቀባዋለሁ።

***pair*** (ፔየ)
ጥንድ/ሁለት ነገሮች ሆነው ለአንድ አገልግሎት የሚውሉ/
I need a new pair of shoes.
አዲስ ጥንድ ጫማዎች እፈልጋለሁ።



*palace* (ፓለስ)
ቤተ-መንግስት/የአገር መሪዎች የሚኖሩበት ቤት/
There are sixty bedrooms in the palace.
ቤተመንግስቱ ውስጥ ስልሣ መኝታ ቤቶች አሉ።

*pale* (ፔይል)
ፈዛዛ/በጣም ደማቅ ያልሆነ ቀለም/
The sky is pale blue today.
ዛሬ ሰማዩ ፈዛዛ ሰማያዊ ነው።

*palm* (ፓ:ም)
1. መዳፍ/የእጅ የውስጠኛው ለስላሳው አካል/
He caught the ball in the palm of his hand.
ኳሷን በእጁ መዳፍ ያዛት።



2. ዘምባባ/ጣፋጭ ቴምር የሚያበቅል ዛፍ/
Dates grow on palm trees.
ቴምሮች በዘንባባ ዛፍ ላይ ይበቅላሉ።




*pan* (ፓን)
መጥበሻ/ስጋ፣አትክልት የሚጠበስበት ሰሃን/
My brother cooked the chicken in the pan.
ወንድሜ የዶሮ ስጋ በመጥበሻ ጠበሰ።



*panda* (ፓንደ)
ትልቅ ድብ የመሰለ ቻይና ውስጥ የሚገኝ እንስሳ
Panda lives in China.
ፓንዳ ቻይና ውስጥ ይኖራል።



*pane* (ፔይን)
መስኮት ላይ የሚገጠም መስታወት
He threw the ball and broke the window pane.
ኳሱን ወርውሮ የመስኮቱን መስታወት ሰበረው።



*pant* (ፓንት)
ማለከለክ/በድካም ቶሎ ቶሎ መተንፈስ
The man was panting after chasing the robber.
ሰውየው ሌባውን ካባረረ በኋላ ሲያለከልክ ነበር።

*pants* ('ፓንትስ)
ሱሪ/ከወገብ በታች የሚለበስ ልብስ/
The boy wore brown pants and a red shirt.
ልጁ ቡና አይነት ሱሪና ቀይ ሸሚዝ ለበሰ።

*paper* ('ፔይፐ)
1. ወረቀት/ለተለያዩ ፅሁፎች መፃፊያ የሚያገለግል/
Paper is made from wood.
ወረቀት ከእንጨት ይሠራል።



2. ጋዜጣ/የተለያዩ ድርጊቶች ታሪኮች አዳዲስ ነገሮች የሚፃፉበት ወረቀት/
My mother reads a paper everyday.
እናቴ ሁልጊዜ ጋዜጣ ታነባለች።



*parachute* ('ፓረሹ:ት)
ዣንጥላ/ከፍ ካለ ቦታ ለምሳሌ ከአይሮፕላን የመዝለያ
When the man jumped from the plane his parachute opened at once.
ሰውየው ከአይሮፕላን ሲዘል የመዝለያ ዣንጥላው ወዲያው ተከፈተ።




*parcel* ('ፓ:ሰል)
በፖስታ ቤት የሚላክ ጥቅል
The parcel arrived in the post this morning.
ጥቅሉ ዛሬ ጠዋት ፖስታ ቤት ደረሰ።



***parent*** ('ፔይረንት)
ወላጆች/የአንድ ሰው እናትና አባት በአንድነት የሚጠሩበት/
His parents love him very much.
ወላጆቹ ልጃቸውን በጣም ይወዱታል።



***park*** (ፓ:ክ)
መናፈሻ/ለመዝናኛ የተዘጋጁ ዛፎች ያሉበት ቦታ/
The park is full of children playing games.
መናፈሻው ጨዋታ በሚጫወቱ ልጆች ተሞልቷል።



***parrot*** ('ፓረት)
በቀቀን/ሰው የሚናገረውን ደግሞ የምትናገር ወፍ/
Some parrots can copy human words.
አንዳንድ በቀቀኖች የሰው ቃላትን መቅዳት ይችላሉ።



***part*** (ፓ:ት)
አካል/የአንድ ነገር ክፍል/
A wheel is a part of a bicycle.
ጎማ የብስክሌት አካል ነው።

***party*** ('ፓ:ቲ)
ድግስ/በተለያዩ ምክንያቶች የሚደረግ ግብዣ/
I am going to a birthday party this week.
በዚህ ሣምንት የልደት ግብዣ እሄዳለሁ።



***pass*** (ፓ:ስ)
አንድ ነገር ለሌላ መስጠት/ ማስተላለፍ /ማቀበል
Pass me the salt, please.
እባክህ ጨውን አቀብለኝ።
I am going to pass the ball to the goalkeeper.
ኳሷን ለጎል ጠባቂው/ለበረኛው ላቀብል ነው።



*passage* (ፓሲጅ)
1. መተላለፊያ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ
This is the passage to the cave.
ይሄ ወደዋሻው የሚወስደው መተላለፊያ ነው።
2. ምንባብ
The passage in the book is interesting.
መፅሀፉ ውስጥ ያለው ምንባብ ደስ የሚል ነው።

*passenger* ('ፓ፡ሲንጀ)
መንገደኛ/በአይሮፕላን በተሽከርካሪዎች፣ የሚጓዝ ሰው/
There were forty passengers in the bus.
በአውቶብሱ ውስጥ አርባ መንገደኞች ነበሩ።

*past* (ፓ፡ስት)
በፊት/ከዛሬ በፊት የነበረ ጊዜ ያለፈ/
In the past we had no radio or television.
በፊት ሬዲዮም ሆነ ቴሌቪዥንን አልነበረንም።


*paste* (ፔይስት)
ማጣበቂያ/አንድ ነገርን ሌላ ላይ የሚያጣብቅ ፈሳሽ/
We made some paste to stick the pictures in our books.
ስእሎቹን መጽሃፎቻችን ላይ ለማጣበቅ ማጣበቂያ ሰራን።

*pastry* ('ፔየስትሪ)
ኬክ/ጣፋጭ ለስላሳ ዳቦ/
My uncle makes pastry.
አጎቴ ኬኮች ይሰራል።




*pat* (ፓት)
ቸብ ቸብ ማድረግ/ትከሻ ወይም ጀርባ ላይ መታ መታ ማድረግ በፍቅር/በጨዋታ
Pat the dog. Then you will be friends.
ውሻውን ቸብ ቸብ አድርገው። ከዛም ጓደኛሞች ትሆናላችሁ።

*patch* (ፓች)
መጣፊያ/ልብስ ሲቀደድ እላዩ ላይ የሚለጠፍ ጨርቅ/
My mother put a patch on my old trousers.
እናቴ አሮጌ ሱሪዬ ላይ መጣፊያ አስገባችልኝ።



***patient*** ('ፔይሽንት)
1. ህመምተኛ/የታመመ ሰው/
There are fifty patients in the hospital.
በሃኪም ቤቱ ውስጥ ሃምሣ ህሙማን አሉ።
2. ታጋሽ/የማይቸኩል እርጋታ ያለው/
He is a patient person. He waited for two hours.
በጣም ታጋሽ ሰው ነው። ሁለት ሰአት ጠበቀ።



***paw*** (ፓ:)
መዳፍ/የእንስሣት እግር የውስጠኛው አካል/
The dog is crying for he has hurt his paw.
ውሻው መዳፉ ስለተጎዳ ይጮሃል።



***pay*** (ፔይ)
መክፈል/ለአንድ ነገር ዋጋ/ገንዘብ መስጠት
I will pay for the book with my own money.
ለመጽሃፉ ከራሴ ገንዘብ እከፍላለሁ።

***pea*** (ፒ:)
አተር/ ትንንሽ ክብ ፍሬ ያለው የጥራጥሬ ዘር/
I like to eat peas and potatoes.
አተርና ድንች መብላት እወዳለሁ።

***peace*** (ፒ:ስ)
ሰላም/ጦርነት፣ረብሻና ብጥብጥ የሌለበት
There will be peace in Africa one day.
አንድ ቀን በአፍሪካ ሰላም ይሆናል።

***peacock*** ('ፒ:ኮክ)
ጣዎስ/በእንግሊዝ የሚገኝ ላባው እጅግ የሚያምር ወፍ/
Look! That peacock is showing his feathers.
ተመልከት! ያ ጣዎስ ላባዎቹን እያሣየ ነው።




***pearl*** (ፐ:ል)
ሉል/አይስተር ከሚባል አሣ ውስጥ የሚገኝ የከበረ ድንጋይ/
Do you know that pearl grows inside oysteres?
ሉል በአይስተር አሣ ውስጥ እንደሚበቅል ታውቃለህ?



*pebble* ('ፔብል)
ወንዝ ዳር የሚገኙ ለስላሳና ትንንሽ ክብ ድንጋዮች/
Don't throw that pebble!
you can hurt someone.
ያንን ድንጋይ አትወርውር! ሰው ልትጎዳ ትችላለህ።



*pedal* ('ፔድል)
ፔዳል/ እንደ ብስክሌት ያሉ ተሽከርካሪዎችን ለማንቀሳቀስ የሚረዳ የእግር መዘውር/
This bicycle is too big. I cannot use the pedals.
ብስክሌቱ በጣም ትልቅ ስለሆነ ፔዳሎቹን መጠቀም አልቻልኩም።



*peel* (ፒ:ል)
መላጥ/የአንድ ነገርን የላይኛውን ሽፋን ማንሣት/
I can peel an orange with my fingers.
በጣቶቼ ብርቱካን መላጥ እችላለሁ።

*pelican* ('ፔሊካን)
ቆልማማሚት/ከውሃ አካባቢ የሚገኙ መንቆራቸው ትልቅ የሆነ ወፎች/ ጳልቃን
Pelican look very strange with their huge beaks.
ከትልቅ መንቁራቸው ጋር ሲታዩ ጳልቃኖች ልዩ ፍጡር ይመስላሉ።




*pen* (ፔን)
1. እስክሪብቶ/ብዕር
I write my letters with my pen.
ደብዳቤዎቼን በብእሬ እጽፋለሁ።




2. የከብቶች ማደሪያ /ጋጣ/
We put the goats in a pen at night.
ሲመሽ ፍየሎቹን ጋጣ አስገባናቸው።

*pencil* ('ፔንሲል)
እርሳስ

Can I use your pencil to draw a house?
የቤት ስእል ለመሳል እርሳስህን መጠቀም እችላለሁ?




(ˈፔንናይፍ)
ሰንጢ/ትንሽ የኪስ የምትተጣጠፍ ቢላዋ/
Cut the paper with your penknife.
በሰንጢህ ወረቀቱን ቅደደው።



(ˈፒ:ፐል)
1. ህዝብ/በአንድነት የብዙ ሰዎች ጥቅል መጠሪያ/
All the people came to see the football team.
ሁሉም ሰዎች የእግር ኳስ ቡድኑን ለማየት መጡ።
2. የአንድ አገር ሰዎች በሙሉ
The number of Ethiopian people reached 65 million.
የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር 65 ሚሊዮን ደረሰ።

*pepper* (ˈፔፐ)
ቃርያ/አረንጓዴ ሆኖ ሾጠጥ ያለ ተክል ሲበሉት የሚያቃጥል/
I like the hot taste of pepper.
የሚያቃጥል ቃሪያ ጣዕም ደስ ይለኛል።



*perch* (ˈፐ:ች)
ቆጥ/ዶሮዎች ለማደር የሚሰፍሩበት እንጨት/
All the hens are on the perch.
ሁሉም ዶሮዎች ቆጡ ላይ ሠፍረዋል።
2. የዓሣ ዝርያ/ ለምግብነት የሚውል



*perfect* (ˈፐ:ፌክት)
ፍፁም/በሁሉም ነገሩ የተሟላ ትክክል የሆነ ነገር/
Nobody is perfect except God.
ከእግዚአብሄር በስተቀር ማንም ፍፁም የለም።

*person* (ˈፐ:ሰን)
አንድ ሰው/ግለሰብ/ ሴት ወይም ወንድ


I know that person she is our neighbour.
ያችን ሰው አውቃታለሁ ጎረቤታችን ናት።



*pet* (ፔት)
ለማዳ/ ለአሜዋችነት የሚያሳድጉት እንስሣ
I have a pet dog. Do you have a pet?
እኔ አሜዋች ውሻ አለችኝ። አንቺስ ለማዳ እንስሳ አለሽ?



*petal* ('ፔትል)
አበባ/ቀንበጥ
The wind has blown all the petals from the flower.
ንፋሱ የአበባውን ቀንበጦች በሙሉ ከአበባው ላይ አራገፋቸው።



*petrol* ('ፔትረል)
ቤንዚን
I will put some petrol in the car today.
ዛሬ መኪናው ውስጥ ነዳጅ እጨምራለሁ።

*photograph* ('ፈውተግራ:ፍ)
ፎቶግራፍ
He took, a photograph of the family.
ቤተሰቡን ፎቶግራፍ አነሣ።



*piano* ('ፒያ:ነው)
ፒያኖ/የሙዚቃ ማጫወቻ/
She plays the piano in school everyday.
ትምህርት ቤት ሁልጊዜ ፒያኖ ትጫወታለች።



*pick* (ፒክ)
ካሉት ነገሮች አንዱን ማንሣት
Pick the biggest orange.

ትልቁን ብርቱካን አንሣ።

*picnic* ('ፒክኒክ)
ሽርሽር/ለእረፍት ከከተማ ወጣ ብሎ ሜዳ ላይ መዝናናት
We are going to picnic tomorrow.
ነገ ሽርሽር እንሄዳለን።



*picture* ('ፒክቸ)
ስእል/ሰው በእጁ የሚሰራው ወይም በካሜራ የሚያነሳው የአንድ ነገር ምስል
He has drawn a picture of a working man.
በስራ ላይ ያለ ሰውን የሚያሳይ ስእል ስሏል።



*pie* (ፓይ)
ሳንቡሳ/ውስጡ ስጋ ወይም አትክልት ያለበት የተጠበሰ ዳቦ/
I love chicken pie for dinner.
ለእራት የዶሮ ሣምቡሣ ደስ ይለኛል።



*piece* (ፒ:ስ)
የአንድ ነገር ቁራጭ
I will eat two pieces of cake.
ሁለት የኬክ ቁራጮች እበላለሁ።



*pig* (ፒግ)
አሳማ/አፍንጫው ወጣ ያለ የሚበላ እንስሣ/
The pig was laying in the mud.
አሣማው ጭቃ ውስጥ ተኝቶ ነበር።



*pigeon* ('ፒጂን)
እርግብ/የቤት ጣራ ስር የምትኖር የወፍ ዘር/
There are lots of pigeons on the roof.
ጣራው ላይ ብዙ እርግቦች አሉ።



*pill* (ፒል)
ኪኒን/በእንክብል መልክ የሚሰጥ መድሃኒት/
My mother gives me two vitamin pills every morning.
እናቴ ሁሌ ጠዋት ጠዋት ሁለት የቫይታሚን ኪኒኖች ትሰጠኛለች።

*pillow* (ˈ ፒለው)
ትራስ/መከዳ/ስንተኛ ራሳችንን የምንደገፍበት ጥጥ ወይም ሌላ ነገር የተሞላ ከረጢት/
I have a soft pillow.
ለስላሣ ትራስ አለኝ።



*pin* (ፒን)
ስፒል/ወረቀቶችን ሰሌዳ ላይ ለማያያዝ እርስ በርስ ለማያ ያዝ የምትረዳ ቀጭን ምስማር/
The pin will hold the papers together.
ስፒል ወረቀቶችን ያያይዛል።




*pinch* (ፒንች)
መቆንጠጥ
I pinched his cheek.
ጉንጩን ቆነጠጥኩት።

*pink* (ፒንክ)
ሮዝ ቀለም
I am wearing a pink dress and my sister is wearing a blue one.
እኔ ሮዝ ቀሚስ ለብሻለሁ። እህቴ ደግሞ ሰማያዊ ቀሚስ ለብሳለች።

*pip* (ፒፕ)
ፍሬ/ፍራፍሬ ውስጥ ያለ የማይበላ ጠንካራ ነገር/
Don't eat the orange pips.
የብርቱካን ፍሬዎች እንዳትበላ።



*pipe* (ፓይፕ)
ቧንቧ/ቱቦ/ውስጡ ክፍት የሆነ ክብና ረዥም ነገር
That pipe brings water to the house.
ያ ቧንቧ ወደ ቤት ውሃ ያመጣል።




*place* (ፕሌይስ)
አንድ ነገር የተቀመጠበት/ያለበት ቦታ
This is the place where I put the box.
ሳጥኑን ያስቀመጥኩበት ቦታ ይህ ነው።

*plain* (ፕሌይን)
ሌጣ/ሌላ ምንም ያልተቀላቀለበት
He wore a plain white shirt.
ሌጣ ነጭ ሸሚዝ ለብሷል።

*plane* (ፕሌይን)
ጠፍጣፋና የተስተካከለ (ለቦታ /ለዕቃ)
Put the egg on the plane table.
እንቁላሉን ጠፍጣፋው ጠረጴዛ ላይ አስቀምጠው።

*planet* (ፕላኔት)
በፀሃይ ዙሪያ የሚዞሩ ዘጠኝ አካላት/ ሜርኩሪ፣ ቬነስ፣ መሬት ማርስ፣ ጁፒተር፣ ሣተርን፣ ኡራነስ፣ ኔፕትዩን፣ ፕሉቶ
Earth is one of the planets.
መሬት ከፕላኔቶቹ አንዷ ናት።



*plant* (ፕላንት)
1. ተክሎች መሬት ላይ የሚበቅሉ ነገሮች/
Trees, bushes and flowers are all plants.
ዛፎች ቁጥቋጦዎችና አበቦች ሁሉም ተክሎች ናቸው።



2. አንድ ነገር መሬት ቆፍሮ መትከል
I planted those flowers last year.
እነዛን አበቦች ባለፈው አመት ተከልኳቸው።



*plastic* (ፕላስቲክ)
ፕላስቲክ/ የተለያዩ ነገሮች መስሪያ ጠንካራ ላስቲክ
I want plastic cup, and plastic dish.
የፕላስቲክ ኩባያ እና የፕላስቲክ ሳህን እፈልጋለሁ።

*plate* (ፕሌይት)
ዝርግ ሰሃን

Put all the meat on the plate.
ሁሉንም ስጋ ዝርግ ሳህኑ ላይ አድርገው።



*play* (ፕሌይ)
1. የስፖርት ውድድር/ጨዋታ
I play table tennis with my sister everyday.
ሁልጊዜ ከእህቴ ጋር የጠረጴዛ ኳስ እጫወታለሁ።
2. ትያትር
My sister and I took part in the school play.
እኔና እህቴ በትምህርት ቤቱ ትያትር ውስጥ ተሳተፍን።

*please* (ፕሊ:ዝ)
እባክህ/የትህትና አነጋገር/
Can I have another piece of cake, please?
እባክህ ሌላ ቁራሽ ኬክ ማግኘት እችላለሁ?

*plenty* ('ፕሌንቲ)
በጣም ብዙ
There is plenty of food for everyone.
ለሁሉም ሰው የሚበቃ በጣም ብዙ ምግብ አለ።

*plough* (ፕላው)
ማረሻ/ገበሬ መሬት የሚያርስበት ከብረትና ከእንጨት የሚሰራ መሣሪያ/
The ox pulled the plough.
በሬው ማረሻውን ጎተተው።



*plug* (ፐለግ)
የመታጠቢያ ቤት የውሃ ማፍሰሻ ቀዳዳ ክዳን
Put the plug in the bath before you turn on the tap.
ቧንቧውን ከመክፈትህ በፊት የገንዳውን ቀዳዳ ክደነው።

*pocket* ('ፖኬት)
ኪስ/ ለአንዳንድ ነገሮች ማስቀመጫ ልብሶች ላይ የሚለጠፍ ከረጢት/
I kept my money in my pocket.
ገንዘቤን ኪሴ ውስጥ አስቀመጥኩት።

*poem* ('ፖዋውየም)
ግጥም/ዜማ ባለው አፃፃፍ አጠር አጠር እየተደረጉ የመጨረሻ ቃላት ድምጽ እንዲመሳሰል ተደርጎ የሚፃፍ ፅሁፍ/
I wrote a poem about our house.
ስለቤታችን ግጥም ፃፍኩ።


*point* ('ፖይንት)
1. ነጥብ/ የአንድ ነገር የመጨረሻው ጫፍ/
An arrow has a sharp point.
ቀስት ሹል ጫፍ አለው።
2. /ማመልከት/ወደ አንድ አቅጣጫ ማሣየት በእጅ
'I live there.' He pointed to a white house.
እዛ ነው የምኖረው ብሎ ወደ አንድ ነጭ

ቤት አመለከተ።
3. በስፖርት ውድድር በፈተና ውጤት የሚሰጥ ማርክ/ዋጋ
Bankoch won the football game and got three points.
ባንኮች የኳስ ግጥሚያውን አሸንፎ ሦስት ነጥብ አገኘ።

***poison*** (' ፖይዝን)
መርዝ/ሲበሉት ወይም ሲጠጡት የሚገድል ነገር/
Don’t drink from that bottle. It might be poison.
ከዛ ጠርሙስ አትጠጣ መርዝ ሊሆን ይችላል።



***pole*** (' ፐውል)
ምሰሶ/ቀጭን ረዥምም ብረት ወይም እንጨት/
There is a flag at the top of that pole.
ከዛ ምሰሶ ጫፍ ላይ ባንዲራ አለ።



***police*** (ፐ' ሊ፡ስ)
ፖሊስ/ሌባ የሚይዝ ሰነሰርአት
የሚያስከብር ሰው/
The police caught the thief in our house.
ፖሊሱ እኛ ቤት የገባውን ሌባ ያዘው።

***pond*** (ፖንድ)
ኩሬ/ከባሕር ወይ ከሃይቅ የሚያንስ አንድ ቦታ የተጠራቀመ ውሃ/
The ducks swim in the pond.
ዳክዬዎቹ በኩሬ ውስጥ ይዋኛሉ።



***pony*** ('ፐውኒ)
ድንክ ፈረስ/ ከሌሎቹ ፈረሶች ቁመቱ አጭር የሆነ ፈረስ
My young sister rides a pony.
ትንሿ እህቴ ድንክ ፈረስ ትጋልባለች።

***pool*** (ፑ፡ል)
ገንዳ/ ለብቻ የተከለለ የመዋኛ ውሃ/
The boy swims in a pool.
ልጁ በገንዳ ውስጥ ይዋኛል።

***poor*** ('ፑወ)
ደሃ/ብዙ ገንዘብ የሌለው ሰው/
I have no clothes or shoes.
I am very poor.
ጫማም ልብስም የለኝም በጣም ደሀ ነኝ።

***popular*** ('ፖፕየለ)
ታዋቂ/ገነኛ/ተወዳጅ/ብዙ ሰው የሚያውቀው የሚወደው
Football is very popular here.

እግር ኳስ እዚህ በጣም ተወዳጅ ነው።

*porridge* (ፖሪጅ)
ገንፎ/ከተፈጨ ጥራጥሬ ዱቄት የሚሠራ የበሰለ የቦካ ዱቄት/
I love porridge for breakfast.
ለቁርስ ገንፎ መብላት ደስ ይለኛል።

*port* (ፖ:ት)
ወደብ/ባህርና መሬት የሚገናኙበት ለመርከብ ማቆሚያ የተሰራ ቦታ/
Mombasa is a large port in Kenya.
ሞምባሳ ኬንያ ውስጥ ትልቁ ወደብ ነው።

*possible* ('ፖሰብል)
ሊሆን ሊደረግ የሚችል ነገር
It is possible for us to swim across that river.
ወንዙን በዋና ማቋረጥ እኛ የምንችለው ነገር ነው።

*post* (ፐውስት)
1. ቋሚ/አጥርን ደግፈው የሚይዙ አልፎ አልፎ የሚተከሉ እንጨቶች/
The posts in our fence are broken.
የአጥራችን ቋሚዎች ተሰብረዋል።




2. ጽሁፍ ደብዳቤ ዕቃ በፖስታ ቤት መላክ
Please post these letters for me.
እነዚህን ደብዳቤዎች እባክህ በፖስታ ቤት ላክልኝ።



*pot* ('ፖ:ት)
እንስራ/ ለፈሳሽ መያዣ ከሸክላ አፈር የሚሰራ ማሰሮ
Those clay pots are beautiful.
የሸክላ ማሰሮዎቹ ቆንጆ ናቸው።

*potato* (ፐ'ቴይተው)
ድንች/ከመሬት ውስጥ ተቆፍሮ የሚወጣ የሚበላ ኩብ ስር/
I like potato with my dinner.
ለራት ድንች ደስ ይለኛል።



*pour* (ፖ:)
ማንቆርቆር/ፈሳሽ ከአንድ ነገር ወደ ሌላ ማፍሰስ/
Pour the milk into the cups.
ወተቱን ኩባያዎቹ ላይ አንቆርቁር።

*powder* ('ፓውደ)
ዱቄት/ደቃቅ የተፈጨ ነገር /ፓውደር/
The powder is in my nose. I am going to sneeze.

ዱቄቱ አፍንጫዬ ውስጥ ገብቷል ሊያስነጥሰኝ ነው።


***power*** ('ፓወ)
አንድን ነገር የሚያንቀሳቅስ ሃይል
The power that makes the lights work is electricity.
መብራቱን እንዲበራ የሚያደርገው ሃይል ኤሌክትሪክ ነው።

***practise*** ('ፕራክቲስ)
አንድን ነገር እየደጋገሙ መስራት/ ለወደፊት በደንብ ለማወቅ መለማመድ
We practise football every week.
በየሳምንቱ እግር ኳስ እንለማመዳለን።

***pray*** (ፕሬይ)
ፀሎት/እግዚአብሔርን ለማመስገን ወይም አንድ ነገር እንዲያደርግልን ለብቻችን የምናደርገው ንግግር
I pray every night before bed.
ከመተኛቴ በፊት ሁልጊዜ ማታ ማታ እፀልያለሁ።




***present*** ('ፕሬዜንት)
1. በአሁኑ ሰአት/በዚህ ጊዜ
At present the school is on holiday.
በአሁኑ ሰአት ትምህርት ቤት ዝግ ነው።
2. ስጦታ/ለበአል፣ ለልደት የሚሰጥ ነገር
I got four presents for my birthday.
ለልደቴ አራት ስጦታዎች አገኘሁ።



***press*** ('ፕሬስ)
አንድን ነገር መጫን
Press the button to ring the bell.
ደወሉን ለመደወል ቁልፉን ተጫነው።

***pretty*** ('ፕሪቲ)
ደስ የሚል/ የሚያምር
She has a pretty face.
የሚያምር ፊት አላት።

***price*** (ፕራይስ)
ዋጋ/አንድን ነገር ለመግዛት የምንከፍለው ገንዘብ
I cannot buy the book because the price is too high.
ዋጋው በጣም ብዙ ስለሆነ መጽሃፉን መግዛት አልችልም።

***pride*** ('ፕራይድ)
መንጋ/በአንድነት የሚሄዱ አንድ አይነት እንስሳት/
The pride of lions killed the antelope.
የአንበሳው መንጋ ድኩላውን ገደለው።

***primary*** ('ፕራይመሪ)
የመጀመሪያ/አንደኛ

Primary school is the first school that you start learning.
አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መጀመሪያ ትምህርት የምትጀምርበት ነው።

*prince* ('ፕሪንስ)
ልኡል/የንጉስ ልጅ/
He is a prince.
እሱ ልኡል ነው።

*print* (ፕሪንት)
ፅሁፍን/ ስእልን በማሽን መፃፍ
We can print the pages of a book on a machine.
የመጽሃፉን ገጾች በማሽን ማተም እንችላለን።

*prison* ('ፕሪዝን)
እስር ቤት/አንድ ሰው ጥፋት ሲሰራ የሚቀመጥበት ቦታ
The police put the thief in prison.
ፖሊሱ ሌባውን እስር ቤት አስገባው።

*prisoner* (ፕሪዝን)
እስረኛ/ ጥፋት ሰርቶ በአንድ ቦታ የተቀመጠ ሰው
The police took the prisoner to the court house.
ፖሊሱ እስረኛውን ወደ ፍርድ ቤት ወሰደው።

*prize* (ፕራይዝ)
ሽልማት/በውድድር ያሸነፈ ወይም በትምህርቱ 1ኛ ለወጣ የሚሰጥ ነገር
The first prize is a bicycle.
የመጀመሪያው ሽልማት ብስክሌት ነው።

*promise* ('ፕሮሚስ)
አንድን ነገር ለማድረግ ቃል መግባት
I promise to work hard.
ጠንክሬ ለመስራት ቃል እገባለሁ።

*pronounce* (ፕረናውንስ)
አንድን ቃል ማንበብ
I can pronounce the word "thought" correctly.
'thought' የሚለውን ቃል በትክክል ማንበብ እችላለሁ።

*pudding* ('ፑዲን)
ከምግብ በሁዋላ የሚበላ ጣፋጭ
My mother makes a nice pudding on Sundays.
እናቴ እሁድ እሁድ ግሩም ጣፋጮች ትሰራለች።

*puddle* ('ፐድል)
አረንቋ/ ዝናብ ሲዘንብ በጎድጓዳ ቦታዎች የሚጠራቀም ውሃ/
It is raining. Look at all the puddles.
ዝናብ እየዘነበ ነው አረንቋዎቹን ተመልከት!

*puff* (ፐፍ)
ማለክለክ/በድካም ቁርጥ ቁርጥ የሚል ትንፋሽ
I always puff when I am running.
ስሮጥ ሁልጊዜ እለከልካለሁ።

*pull* (ፑል)
መጎተት/ወደ ራስ መሣብ
Magnet pulls irons.
ማግኔት ብረቶችን ወደራሱ ይስባል።



*pump* (ፐምፕ)
ፓምፕ/በኤሌክትሪክ ሃይል ወይም በእጅ እየዞረ ከጉድጓድ ውሃ መሳቢያ ወይ አየር መግፊያ መግሪያ/
The farmers bought an electric pump.
ገበሬዎቹ የኤሌክትሪክ ፓምፕ ገዙ።

*punch* (ፐንች)
በቡጢ/እጅን ጨብጦ መምታት/
Don't punch him in the face.
ፊቱን በቡጢ አትምታው።

*puncture* ('ፐንክቸ)
የመኪና ወይም የብስክሌት ጎማ ቀዳዳ
A piece of glass put a puncture in my bicycle tyre.
ቁራጭ መስታወት የብስክሌት ጎማዬን ቀደደው።

*pupil* ('ፐዩ:ፐል)
ተማሪ
The pupils in this class are all very good.
የዚህ ክፍል ተማሪዎች በሙሉ በጣም ጥሩዎች ናቸው።

*puppet* ('ፐፒት)
አሻንጉሊት/ከጭቃ ወይ ከፕላስቲክ የሚሠራ የውሸት ሰው
That puppet looks alive.
ያ አሻንጉሊት ህይወት ያለው ይመስላል።



*puppy* ('ፐፒ)
ቡችላ/ የውሻ ልጅ
The dog has three lovely puppies.
ውሻዋ ሶስት የሚያማምሩ ቡችሎች አሏት።



*purse* (ፐ:ስ)
ከረጢት/ሚጢጢ የገንዘብ ቦርሳ
My sister keeps all her money in her purse.
እህቴ ገንዘቧን በሙሉ የገንዘብ ቦርሳዋ ውስጥ ታስቀምጣለች።

*push* ('ፑሽ)
መግፋት
My bicycle has a puncture.
I will push it home.
ብስክሌቴ ጎማው ስለተበሳ እየገፋሁ ወደቤት እወስደዋለሁ።


*put* (ፑት)
ማስቀመጥ/አንድን ነገር አንድ ሌላ ነገር ላይ ወይም ውስጥ መክተት
He put all the pieces of paper in the fire.
ቁርጥራጭ ወረቀቶቹን በሙሉ እሣት ውስጥ ከተተ።

*puzzle* ('ፐዘል)
እንቆቅልሽ/ በቀላሉ ለማወቅ የማይቻል ጥያቄ
In this puzzle you pick the right picture.
እዚህ እንቆቅልሽ ውስጥ ትክክለኛውን ስእል ትመርጣለህ።

*pygmy* ('ፒግሚ)
ፒግሚ/በጣም አጭር የሆነ/
The pygmy hippopotamuses are very small.
የፒግሚ ጎማሬዎች በጣም ትንንሾች ናቸው።

*pyjamas* (ፐ'ጃ:መዝ)
ፒጃማ/ማታ ማታ ስንተኛ የምንለብሰው ልብስ/
I wear my blue pyjamas in bed every night.
ሁሌ ስተኛ ሰማያዊውን ፒጃማዬን እለብሣለሁ።

*pyramid* ('ፒረሚድ)
ፒራሚድ/ከስሩ ሰፋ ብሎ እየጠበበ የሚሄድ ቅርጽ
There are big pyramids in Egypt.
በግብፅ ውስጥ ትልልቅ ፒራሚዶች አሉ።



*Python* ('ፓይተን)
ዘንዶ/እንደ እባብ በደረቱ የሚሣብ ግዙፍና ሃይለኛ እንስሣ/
Look! That python must be six metres long.
ተመልከት ያ ዘንዶ ቁመቱ ስድስት ሜትር መሆን አለበት።



# Qq

*Q,q* (ክዩ፡)
17ኛው የእንግሊዝኛ ፊደል

*quarrel* ('ክዎረል)
መጨቃጨቅ/ በአንድ ነገር
ሳይስማሙ ከቀሩት ሰው ጋር በቁጣ
መነጋገር/መጣላት/
They quarrelled over the bicycle.
በብስክሌቱ ምክንያት ተጣሉ።

*quarry* (ክዎሪ)
ሰዎች ውድ ድንጋዮች/ወርቅ ለማውጣት
የሚቆፍሩት ጉድጓድ
They got those big pieces of stone from the quarry.
እነዚያን ትልልቅ ሰብርባሪ
ድንጋዮች ከጉድጓዱ ውስጥ አገኙ።

*quarter* (ክዎተ)
ሩብ/አንድ ነገር ለአራት ቦታ እኩል
ተከፍሎ ከተከፈሉት ከአራቱ አንዱ/
We are four and we can take a quarter each.
አራት ነን ስለዚህ እያንዳንዳችን ሩብ
ሩብ መውሰድ እንችላለን።

*queen* (ክዊ፡ን)
ንግስት/የንጉስ እናት ወይም ሚስት
ወይም የነገሰች ሴት
Queen Tayitu was one of the most famous queens of Ethiopia.
ንግስት ጣይቱ ከታወቁ የኢትዮጵያ
ንግስቶች አንዷ ነበረች።

*question* ('ክዌስችን)
ጥያቄ/ያላወቅነውን ነገር ለማወቅ
የምንጠይቀው
What is your name? The teacher asked me.
አስተማሪው ስምሽ ማነው ብለው ጠየቁኝ?

*queue* ('ክዩ)
ሰልፍ/አንድ ቦታ ለመግባት
ተከታትሎ መቆም
There is a queue outside the new shop.
አዲሱ ሱቅ ውጪ ሰልፍ አለ።




*quick* (ክዊክ)
ፈጣን እንቅስቃሴ
Be quick your father is waiting.
አባትህ እየጠበቀህ ነው ፈጠን በል።

*quiet* (ክዋየት)
ፀጥ ያለ/ ምንም ድምጽ የማይሰማበት
My house is always quiet.
ቤቴ ሁልጊዜ ፀጥ ያለ ነው።

*quiz* (ክዊዝ)
የጥያቄና መልስ ጨዋታ
Every Friday, the teacher gives a Geography quiz.
መምህሩ በየሣምንቱ አርብ የስነምድር
ትምህርት ጥያቄና መልስ ጨዋታ
ያደርጋሉ።

*R,r* (አ፡)
የእንግሊዝኛ አስራ ስምንተኛው ፊደል

*rabbit* ('ራቢት)
ጥንቸል
Rabbits live in holes in the ground.
ጥንቸሎች የሚኖሩት ከመሬት ውስጥ ባለ ጉድጓድ ውስጥ ነው።



*race* (ሬይስ)
እሽቅድምድም/ የሩጫ የፍጥነት ውድ ድር
I will race you to the classroom.
እስከ ክፍል ድረስ ሩጫ እሽቀዳደምሃለሁ።

*racket* ('ራኬት)
ራኬት/ የጠረጴዛ ኳስ/የሜዳ ቴኒስ ጨዋታ ላይ ኳሷን መምቻ አናቱ ክብ ሆኖ መያዣ ያለው/
He hit the ball hard with his racket.
በራኬቱ ኳሷን አክርሮ መታት።



*radio* ('ሬይዲየው)
ሬዲዮ/እቤታችን ሆነን የተለያዩ ንግግሮችንና ሙዚቃዎችን የምንሠማበት መሣሪያ/
I listen to the radio everyday.
በየቀኑ ሬዲዮ እሰማለሁ።



*radius* ('ሬይዲየስ)
ሬዲየስ/በአንድ ክብ ከመሀሉ እስከ ዳሩ ድረስ ያለው ርቀት/
This circle has a radius of six centimetres.
የዚህ ክብ እስከ መሃሉ ያለው ርቀት ስድስት ሣንቲሜትር ነው።



*raft* (ራ፡ፍት)
ታንኳ/እንጨት ተቦርቡሮ ተገጣጥሞ የሚሠራ የውሃ ላይ መጓጓዣ/
The boys sailed across the river on the raft.
ልጆቹ በታንኳ ወንዙን አቋረጡ።



(ራግ)
ቡትቶ/የተቀራረጠ ጨርቅ/
My father wiped his dirty hands on a rag.
አባቴ የቆሸሸ እጁን በቡትቶ ጠረገ።

(ሬይጅ)
ቁጣ
The teacher is in a rage.
አስተማሪዋ ተቆጥተዋል።

(ሬይል)
ሃዲድ/ባቡር የሚሄድበት የብረት መንገድ/
Trains run on rail.
ባቡሮች በሃዲድ ላይ ይሄዳሉ።



(ሬይን)
ዝናብ/ከሰማይ የሚወርድ ውሃ/
It needs rain to make the corn grow.
በቆሎው እንዲያድግ ዝናብ ያስፈልገዋል።



(ረይዝ)
አንድን ነገር ወደ ላይ ማንሣት
Will you help me to raise this heavy stone?
ይህን ከባድ ድንጋይ ወደ ላይ ለማንሣት ታግዘኛለህ?

('ሬይዝን)
ዘቢብ/የደረቀ ወይን
My brother put some raisins in the cake.
ወንድሜ ኬኩ ውስጥ ጥቂት ዘቢብ ጨመረበት።

(ሬይክ)
ከደረቅ የዘንባባ ቅጠል የሚሰራ መጥረጊያ
Give me the rake. I will clear up the leaves.
መጥረጊያውን ስጠኝ። ቅጠሎቹን እጠርጋቸዋለሁ።



*ram* (ራ·ም)
በግ /ወንድ በግ/
Rams have large horns.
ወንድ በጎች ትልልቅ ቀንዶች አሏቸው።



*ranch* (ራ፡ንች)
የከብት እርባታ/ እርሻ ማቢያ/
My uncle has a ranch near here.
አጎቴ እዚህ አካባቢ የከብት እርባታ አለው።

*rapid* ('ራ·ፒድ)
አንድን ነገር በፍጥነት ማድረግ
The firemen moved rapidly into the burning house.
የእሳት አደጋ ተከላካዮቹ በፍጥነት ወደሚቃጠለው ቤት ሄዱ።

*rare* (ሬየ)
ብርቅ/ አይነቱ ብዙ ያልሆነ ጥቂት በመሆኑ ብርቅ የሆነ
Red fox is a rare animal.
ቀይ ቀበሮ ብርቅ እንስሣ ናት።



*rascal* ('ራ፡ስከል)
ባለጌ/እናት አባቱን የማያከብር የማይታዘዝ ልጅ/
My mother says my brother is a rascal because he disobeys her.
እናቴ ወንድሜ ስለማይታዘዛት ባለጌ ነው ትላለች።

*rash* (ራ·ሽ)
ሽፍታ/ሰውነት ላይ የሚወጣ ትንንሽ ነገሮች/
The doctor gave her pills for her rash.
ሃኪሙ ለሽፍታዋ ኪኒን ሰጣት።

*rat* (ራ·ት)
አይጥ
The rat is in the bin eating the corn.
አይጡ ጎተራ ውስጥ በቆሎ እየበላ ነው።



*rattle* ('ራትል)
ማንኳኳት/ነገሮችን በማጋጨት ድምፅ መፍጠር/
Shake those stones in the tin. They will rattle.
ቆርቆሮ ውስጥ ያሉትን ድንጋዮች ወዝውዛቸው ይንኳኳሉ።

*raven* ('ሬይቭን)
**ቁራ/ጥቁር አሞራ**
Ravens are very noisy birds.
**ቁራዎች ጯሂ ወፎች ናቸው።**




*raw* (ሮ፡)
**ጥሬ/እሣት ያልነካው/ ያልበሰለ/**
I like to eat raw carrots.
**ጥሬ ካሮት መብላት እወዳለሁ።**

*ray* (ሬይ)
**ጮራ/ከፀሃይ የሚወረወር ብርሃን/**
The sun's rays came through the window.
**የፀሃይ ጨረር በመስኮቱ ገባ።**

*reach* (ሪ፡ች)
**አንድ ቦታ መድረስ**
When we reach home we will have a cup of tea.
**እቤት ስንደርስ አንድ ስኒ ሻይ እንጠጣለን።**

*read* (ሪ፡ድ)
**ማንበብ**
I like to read story books.
**የተረት መጻህፍትን ማንበብ ያስደስተኛል።**



*ready* ('ሬዲ)
**መዘጋጀት/አንድ ነገር ለማድረግ በቅድሚያ የሚያስፈልገውን ሰርቶ መጨረስ/**
We are ready to go to the cinema.
**ሲኒማ ለመሄድ ተዘጋጅተናል።**

*real* ('ሪ፡የል)
**እውነተኛ /ውሸት ያልሆነ/**
Are those flowers in that vase real?
**እነዛ አበባ ማስቀመጫ ውስጥ ያሉት አበቦች እውነተኛ አበቦች ናቸው?**

*rear* (ሪየ)
**ከሁሉ ሁዋላ መጨረሻ**
The baby donkey walked at the rear of the herd.
**ውርንጭላዋ ከመንጋው መጨረሻ ሄደች።**

*reason* ('ሪ፡ዝን)
**አንድን ድርጊት የፈፀምንበት ምክንያት**
The reason I am late is because my car broke down.
**ያረፈድኩበት ምክንያት መኪናዬ ስለተሰበረች ነው።**


*receive* (ሪ'ሲ:ቭ)
ከሌላ ሰው አንድን ነገር መቀበል/ መረከብ/
He received the prize for his good work.
ለጥሩ ስራው ሽልማት ተቀበለ።

*recess* (ሪሰስ)
እረፍት/ ለአጭር ጊዜ የሚደረግ።
"We are tired we want a recess", shouted the boys.
ልጆቹ"ደክሞናል እረፍት እንፈልጋለን" ብለው ጮሁ።


*recipe* ('ሬሲ.ፒ)
ስለ አንድ ምግብ መጠጥ አሠራር የሚገልጽ ፁሁፍ/መመሪያ/
I have a recipe for fruit cake.
የፍራፍሬ ኬክ አሠራር መመሪያ አለኝ።

*recognise* ('ሬከግናይዝ)
ማስታወስ/አንድ ቀድመው ያዩትን ወይም የሚያውቁትን ነገር ደግመው ሲያዩት ማወቅ መቻል/
The farmer recognised the man who had stolen his cattle.
ገበሬው ከብቶቹን የሰረቀውን ሰው አስታወሰው።

*record* (ሬኮ:ድ)
1. በቴፕ ክር ወይም በሸክላ የታተመ ዘፈን
This record makes me want to dance.
ይህ ዘፈን ደንስ ደንስ አሰኘኝ።
2. ስለ አንድ ነገር ድርጊት ተመዝግቦ የተቀመጠ መረጃ/ ፋይል
You can get his address in his record.
አድራሻውን በፋይሉ ውስጥ ልታገኘው ትችላለህ ።



*rectangle* ('ሬክታ:ንግል)
አራት ቀጥተኛ መአዘንና ጎኖች ያሉት ቅርፅ
A football field is the shape of a rectangle.
የእግር ኳስ ሜዳ ቅርፅ አራት መአዘን ነው።



*red* (ሬድ)
ቀይ/ደም የመሰለ ቀለም
My sister is wearing a red dress.
እህቴ ቀይ ቀሚስ ለብሳለች።


*referee* (ሬፈ'ሪ:)
ዳኛ/አንድን የስፖርት ውድድር ተመልክቶ ፍርድ የሚሰጥ ሰው
The referee sent the player off for fighting.
ዳኛው ተጫዋቹ ስለተደባደበ ከሜዳ አስወጡት።



*reflection* (ሪ'ፍሌክሽን)
ነፀብራቅ/በመስታወት ወይም በውሃ ውስጥ የምናየው ምስል/
You can see the reflection of the trees in the water.
የዛፎቹን ነፀብራቅ በውሃ ውስጥ ማየት ትችላለህ።



*refrigerator* (ሪ'ፍሪጀሬይተ/ር)
ማቀዝቀዣ/ውስጡ የሚቀመጡ ነገሮችን የሚያቀዘቅዝ መሣሪያ
My mother put the milk in the refrigerator.
እናቴ ወተቱን ማቀዝቀዣ ውስጥ አስቀመጠችው።



*reign* ('ሬይን)
መንገስ/መግዛት/ንጉሶች የአንድ አገር ገዢ ሆኖ የቆዩበት ጊዜ/ዘመነ መንግስት
The king has reigned for twenty years.
ንጉሱ ለሃያ አመታት ነገሱ።

*rein* (ሬን)
ልጓም/በፈረሶች ሲጋለብ ወይም ጋሪ ሲጎተት ፈረሶቹን ለመቆጣጠር አፋቸው ላይ የሚታሠር ገመድ/
Do not pull the reins hard. You will hurt the horse's mouth.
የፈረሱን አፍ ልትጎዳው ስለምትችል ልጓሙን በሃይል አትጎትት።



*relative* ('ሬለ'ቲቭ)
ዘመድ/የእናት እና የአባት ቤተሰቦች/
አጎቶች አክስቶች በሙሉ/
Only our relatives are coming to the party.
የኛ ዘመዶች ብቻ ለድግሱ ይመጣሉ።

*remember* (ሪ'ሜምበ)
ማስታወስ/አንድን ነገር አለመርሳት/
I must remember to lock the door.
በሩ መቆለፉን ማስታወስ አለብኝ።

*remove* (ሪ'ሙ፡ቭ)
ከአንድ ቦታ ማንሳት ማውጣት
Please remove your goats from my field.
እባክህ ፍየሎችህን ከሜዳዬ አውጣ።

*repeat* (ሪ'ፒ፡ት)
መድገም
Repeat the word after me.
ቃሉን ከኔ ቀጥላችሁ ድገሙት።

*reptile* ('ሬፕታይል)
በደረቱ የሚሳብ ፍጡር/እባብ ወዘተ.../
Snakes, lizards and crocodiles are all reptiles.
እባቦች፣ እንሽላሊቶች እና አዞዎች በደረታቸው የሚሳቡ ናቸው።



('ሬስክዩ፡)
ከአንድ ሊደርስ ከሚችል ጉዳት ማዳን
The policeman rescued the girl from the burning house.
ፖሊሱ ልጅቷን ከሚነደው ቤት አደጋ አዳናት።


(ሬስት)
1. ስራ አለመስራት/ማረፍ/ መተኛት
The dog rested under the tree.
ውሻው ከዛፉ ስር አረፍ አለ።
2. ትርፍ/አንድ ነገር ስራ ላይ ውሎ የተረፈው/
Dad put the rest of the cake in a big tin.
አባዬ የተረፈውን ኬክ ትልቅ ጣሳ ውስጥ ከተተው።

(ሪዘልት)
በአንድ ድርጊት ምክንያት የሚፈጠር ነገር/ውጤት/
The accident was the result of bad driving.
አደጋው የመጥፎ አነዳድ ውጤት ነበር።

(ሪዎ፡ድ)
ሽልማት/አንድ ጥሩ ስራ ለሠራ ሰው የሚሰጥ
Genene got a reward for putting out the fire.
ገነነ እሳቱን ስላጠፋ ሽልማት ተሰጠው።


(ራይኖ'ሰረስ)
አውራሪስ/አፍንጫው ላይ ቀንድ ያለው ግዙፍ የዱር እንስሳ/

Rhinoceroses have horns on their noses.
አውራሪሶች አፍንጫቸው ላይ ቀንድ አላቸው፡፡



*rhyme* ('ራይም)
ቤት የሚመቱ/የመጨረሻ ፊደላቸው ድምፅ የሚመሳሰል ቃላት/
Cat rhymes with mat.
ካት እና ማት ቤት ይመታሉ፡፡

*rib* (ሪብ)
ጎድን/ደረታችን ላይ ያለ የተያያዘ አጥንት/
He fell off the roof so one of his ribs is broken.
ከጣራው ወድቆ አንድ ጎድኑ ተሠበረ፡፡



*ribbon* ('ሪበን)
ሪቫን/ሴቶች ፀጉራቸውን የሚያስሩበት ጨርቅ/
She wore a red ribbon in her hair.
ፀጉሯ ላይ ቀይ ሪቫን አሰራለች፡፡



*rice* (ራይስ)
ሩዝ/ነጫጭ ትንንሽ ፍሬዎች ያሉት የጥራጥሬ ዘር/
Rice grows in hot, wet places.
ሩዝ በሞቃታማ ርጥብ ቦታዎች ይበቅላል፡፡

*rich* (ሪች)
ባለፀጋ/ሀብታም/ብዙ ገንዘብ ያለው ሰው፡፡
The rich man lives in a large house.
ሀብታሙ ሰው በትልቅ ቤት ውስጥ ይኖራል፡፡


*ride* (ራይድ)
1. መጋለብ/በፈረስ ወይም በብስክሌት መሄድ/
I can ride a horse.
ፈረስ መጋለብ እችላለሁ፡፡



2. መሸኘት/በግል መኪና ሌላ ሰው አሳፍሮ መውሰድ/
Dad will give us a ride to the shops in his car.

አባዬ በመኪናው እስከ ሱቅ ድረስ ይሸኘናል።

*rifle* ('ራይፍል)
ጠመንጃ/ሜፉ ክብ ቀዳዳ ያለው ረጅም የጦር መሳሪያ/
The man shot the lion with his rifle.
ሰውየው በጠመንጃው አንበሳውን ገደለው።



*right* (ራይት)
1. ትክክል
This is the right way to play basketball.
ቅርጫት ኳስ ለመጫወት ትክክለኛው መንገድ ይህ ነው።
2. ቀኝ
Most people write with their right hand.
ብዙ ሰዎች በቀኝ እጃቸው ይፅፋሉ።

*ring* (ሪን)
ቀለበት/ክብ የጣት ጌጥ
My mother wears a gold ring on her finger.
እናቴ ጣቷ ላይ የወርቅ ቀለበት ታደርጋለች።



2. መደወል ብረትን በማጋጨት ድምፅ መፍጠር/
The church bell rings every Sunday.
የቤተክርስቲያኑ ደወል በየሣምንቱ እሁድ ይደወላል።



*rinse* ('ሪንስ)
ማለቅለቅ/ልብስ አጥቦ መጨረሻ ላይ በንፁህ ውሃ መንከር/
I will rinse the shirt in the basin.
ገንዳው ውስጥ ሸሚዙን አለቃልቀዋለሁ።

*rip* (ሪፕ)
መቦጨቅ/ በጥርስ ነክሶ መሣብ
The dog ripped the boy's trousers with its teeth.
ውሻው የልጁን ሱሪ በጥርሱ ቦጨቀው።

*ripe* ('ራይፕ)
የበሰለ/ለመበላት የደረሰ ፍሬ/
The bananas are ripe enough to eat.
ሙዞቹ ለመበላት ደርሰዋል።

*rise* (ራይዝ)
ከተደበቁበት ወይም ከነበሩበት መውጣት
The sun rises at the same time everyday.
ፀሃይ በየቀኑ በተመሣሣይ ሰአት ትወጣለች።



*river* ('ሪቨ)
ወንዝ/ትልቅ ረዥም የሚወርድ ውሃ/
There are several fish in the river.
በወንዙ ውስጥ ብዙ አሳዎች አሉ።



*road* (ረውድ)
መንገድ/አንድን ከተማ ከሌላው የሚያገናኝ ለመኪና መሄጃ የሚሠራ ቦታ/
They are building a new road to the next village.
ወደሚቀጥለው ሰፈር የሚያደርስ አዲስ መንገድ እየሰሩ ነው።



*roar* (ሮ፡)
ግሣት/የአንበሳ ጩኸት/
We can hear the roar of the lions.
የአንበሶቹን ግሳት መስማት እንችላለን።


*roast* (ረውስት)
መጥበስ
My father is roasting the meat in the oven for dinner.
አባቴ ለእራት ስጋውን በምድጃ እየጠበሰ ነው።

*rob* (ሮብ)
መዝረፍ/የሰው የሆነን ነገር በግድ በጉልበት መውሰድ/
He robbed me of all my money.
ገንዘቤን በሙሉ ዘረፈኝ።

*robe* (ረውብ)
መጎናፀፊያ ወይም ካባ/ከልብስ በላይ የሚለበስ ዘርፋፋ ጩርቅ/
Judges wear robes.
ዳኞች ካባ ይለብሳሉ።



*robot* (ረውቦት)
ሮቦት/ብዙ ሥራዎችን ሰውን ተክቶ የሚሰራ ማሽን/
Many cars are now made by robots.
በአሁኑ ግዜ ብዙ መኪናዎች በሮቦት ይሰራሉ።




*rock* (ሮክ)
1. አለት/በጣም ትልቅ ድንጋይ/
A large rock rolled down from the mountain.
ከተራራው ላይ ትልቅ አለት ተንከባለለ።



2. መወዝወዝ
She rocked the baby to stop it from crying.
ህፃኑ ማልቀሱን እንዲያቆም ወዘወዘችው።

*rocket* (ሮኪት)
በጣም በከፍተኛ ፍጥነት አየርን እየሰነጠቀ የሚጓዝ ተሽከርካሪ
This rocket is going to the moon.
መንኮራኩሩ ወደ ጨረቃ ሊጓዝ ነው።



*rod* (ሮድ)
በትር/ቀጭን ረጅም እንጨት/
The old man has a strong rod.
ሽማግሌው ጠንካራ በትር አላቸው።

*roll* (ረውል)
መንከባለል
He rolled all the way down the hill.
ከተራራው ጫፍ ጀምሮ እስከታች ተንከባለለ።

*roof* (ሩ፡ፍ)
ጣራ/የቤት ክዳን
We put a new roof on the house.
ለቤቱ አዲስ ጣራ አስገባንለት።




*rooster* (ሩ:ስተ)
አውራ ዶሮ/ወንድ ዶሮ
Roosters make a lot of noise in the morning.
አውራ ዶሮዎች ጠዋት ጠዋት በጣም ይጮሃሉ።




*room* (ሩ:ም)
በቤት ውስጥ ራሱን የቻለ አንድ ክፍል
Kitchens and bedrooms are all rooms.
ማዕድቤቶችም መኝታቤቶችም ሁሉም ክፍሎች ናቸው።

*root* (ሩት)
ስር/የእፅዋት የዛፎች መሬት ውስጥ ያለው አካል/
Some plants have roots that you can eat.
አንዳንድ እፅዋት ስራቸው ይበላል።



*rope* (ረውፕ)
ገመድ/አንደ ላይ የተገመደ ነገር በተለይ ከክር ወይም ከቃጫ የሚሠራ/
The rope is broken when they are pulling it.
ገመዱን ሲጎትቱት ተበጠሰ።




*rot* (ሮት)
መበስበስ/ በጣም በስሎ መበላሸት የጀመረ ፍሬ/
This fruit is starting to rot. We cannot eat it.
ይህ ፍሬ መበስበስ ጀምሯል። ልንበላው አንችልም።


*rough* (ሩፍ)
1. ሸካራ/አካሉ ለስላሣ ያልሆነ/
This wood is too rough to make a nice table.
ይህ እንጨት በጣም ሸካራ ነው። ጥሩ ጠረጴዛ ለመስራት አይሆንም።

2. ፀባዩ ጥሩ ያልሆነ ስርአት የሌለው ሰው።
Do not play with that boy. He is rough.
ከዛ ልጅ ጋር አትጫወት ስነስርአት የለውም።

*round* (ራውንድ)
ክብ/የ0 ቅርጽ ያለው/
We have a round table in our kitchen.
ማድቤታችን ውስጥ ክብ ጠረጴዛ አለን።



*row* (ራው)
1. በተርታ/አንድ መስመር ይዞ መቀመጥ ወይም መቆም
The children sat in rows.
ልጆቹ በተርታ ተቀመጡ።



2. ጀልባን መቅዘፍ
Eight men row this big boat.
ይህን ትልቅ ጀልባ ስምንት ሰዎች ይቀዝፉታል።

*rub* (ረብ)
ለመጠራረግ ወይም ለመቀባት ሰውነትን በእጅ መንካት/ መዳበስ
My mother rubbed cream into my face.
እናቴ ፊቴን ቅባት ቀባችኝ።

*rubber* (ረበ)
1. ጎማ/ከዛፍ ወተት የሚሰራ/ጠንካራ ወፍራም ላስቲክ/
Rubber is obtained from the rubber tree.
ጎማ የሚገኘው ከጎማ ዛፍ ነው።



2. ላጲስ
I used a rubber to clean my hand writing.
የእጅ ፅሁፌን ለማጥፋት ላጲስ ተጠቀምኩ።

*rubbish* (ረቢሽ)
ቆሻሻ/ተጠቅመን የምንጥለው እቃ
The men come every Tuesday to collect the rubbish.
በየሣምንቱ ማክሰኞ ቆሻሻ ለመሰብ ሰብ ሰዎች ይመጣሉ።

*rude* (ሩ:ድ)
በሃይል በቁጣ መናገር/ ትህትና የሌለው ንግግር
She spoke rudely to her father.
አባቷን በቁጣ ተናገረች።

*rug* (ረግ)
*ምንጣፍ/መሬት ላይ የሚነጠፍ ቁራጭ ጨርቅ/*
There is always a piece of rug in front of the door.
ከበሩ ፊት ለፊት ሁልጊዜ ምንጣፍ አለ።



*rule* (ሩ፡ል)
*ሥርዓት/አንድ ነገር የሚሠራበት መመሪያ*
You must come to school on time. That is a rule.
ትምህርት ቤት በሰአቱ መምጣት አለብህ! ይህ መመሪያ ነው።

*ruler* ('ሩ፡ለ)
1. የአንድ አገር መሪ/ገዢ
Daniel Arap Moi is the ruler of Kenya.
ዳንኤል አራፕ ሞይ የኬንያ መሪ ናቸው።
2. ማስመሪያ
I took my ruler to school with me.
ማስመሪያዬን ወደ ትምህርት ቤት ወሰድኩ።

*run* (ረን)
*መሮጥ*
Can you run as fast as I can?
እንደኔ በፍጥነት መሮጥትችላለህ?



*rush* (ረሽ)
*መጣደፍ/ቶሎ ቶሎ መሄድ/*
We all rushed across the road to catch the bus.
ሁላችንም አውቶብስ ለመያዝ በጥድፊያ መንገዱን አቋረጥን።

*rust* (ረስት)
ዝገት/ብረት እርጥበት ሲነካው የሚፈጠር ቡና አይነት ነገር/
The bridge over the river is brown with rust.
ከወንዙ ላይ ያለው ድልድይ በዝገት ቡናማ ሆኗል።

